# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

***በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የንበባ ክሂል ውጤት ተዛምዶ ፍተሻ፤***

*(በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)* አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፣

በ

አስራት አሠፋ

ግንቦት፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

*በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የንበባ ክሂል ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ፍተሻ፤ (በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛ እና መሠናዶ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)*

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፣

በ

አስራት አሠፋ

ዋና አማካሪ፡- ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- ማንያለው አባቴ (ዶ/ር)

ግንቦት፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# የአማካሪዎች ይሁንታ

ተማሪ አስራት አሠፋ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ ሲሆን የመመረቂያ ጥናቱን ከአማካሪዎቹ ጋር በትብብር እየሰራ የቆየ ስለሆነ ለተቋሙ መቅረብ የሚችል መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

ዋና አማካሪ ስም፡- -------------------- ፊርማ ------------------- ቀን ----------------

ረዳት አማካሪ ስም ፡- ------------------ ፊርማ---------------------- ቀን--------------

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የንበባ ክሂል ውጤት ተዛምዶ ፍተሻ፤ (በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ **በአስራት አሠፋ** የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኝ ቦርድ አባላት ተረጋግጧል፡፡

1. የአማካሪ ስም፡-____________________________

   ፊርማ፡-____________________

   ቀን፡- ____________________

1. የውስጥ ፈታኝ ስም፡-____________________________

   ፊርማ፡-__________________

   ቀን፡- ____________________

2. የውጭ ፈታኝ ስም፡-____________________________

   ፊርማ፡-___________________

   ቀን፡- ____________________

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ ፍተሻ በዘጠነኛ (9ኛ) ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ሲሆን የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መደረጋቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ______________________________

ፊርማ፡- _______________

ቀን፡-_______________

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም በነገር ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን። በመቀጠል ከርዕስ መረጣው ጀምሮ እስከ ሥራዪ ማጠናቀቂያ ድረስ ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት፣ ስህተቶቼን በማረም፣ ለሥራዪ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር) እና ለረዳት አማካሪዬ ማንያለው አባቴ (ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

እንዲሁም ለዚህ ጥናት ስኬት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ድጋፍ ላደረጉልኝ ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማስተባበር፣ ፈተናውንና የጽሑፍ መጠይቆችን በማረምና ተገቢ አስተያየቶችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለመምህርት ቆንጅት ተክሌ፣ ለፈተናውና ለጽሑፍ መጠይቅ ሥራው ውድ ጊዜያቸውን ሰጥተው መረጃ ለሰጡኝ ለዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ምስጋናዬ የላቀ ነው።

በመጨረሻም የጽሕፈት መሳሪዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ፣ እንዲሁም ከህሊና ዝግጅት ጀምሮ በሁሉ ከጎኔ ያልተለዩኝ ለውድ ባለበቴ ብርቅነሽ ንጋቱ፣ ለልጆቼ አብሥራ አስራትና ቃል አብ አስራት እና ጓደኛዬ አስታራቂ ምትኩ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

## ማውጫ

ይዘት ገጽ


ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ 1

ምዕራፍ አንድ፤ ........ 2

መግቢያ ........ 2

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 6

1.3. የጥናቱ መላምቶች ........ 8

1.4. የጥናቱ ዓላማ ........ 8

1.4.1. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ........ 8

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 8

ሀ. ተማሪዎቹ በጥናቱ ውጤት ........ 8

ለ. በሁለተኛ (አማርኛ) ቋንቋ ትምህርት ........ 8

ሐ. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ........ 9

መ. የአማርኛ ቋንቋን ........ 9

ሠ.ለስርዓተ-ትምህርት ........ 9

ረ. በሁለተኛ ቋንቋ ........ 9

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 9

1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ ........ 10

ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 11

2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........ 11

2.1.1. የፍላጎት ምንነትና ጽንሰ ኃሳባዊ መሰረቶች ........ 11

2.1.2. የፍላጎት ተኮር ትምህርት አስፈላጊነት ........ 12

2.1.3. ፍላጎት ተኮር ትምህርትን ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማቅረብ ጠቀሜታ ........ 12

2.2. የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጠበቅ የሚረዳ ብልሃቶች ........ 13

2.3. የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ግንኙነት/ተዛምዶ ........ 14

2.4. በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎቹ ዘንድ ለማስረጽ የቋንቋ መምህራን ሚና 15
2.4.1. ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብን በፍላጎት እንዲያዳብሩ ማድረግ። .......... 15
2.4.2. ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎት በውስጣቸው ማስረጽ 15
2.4.3. ተማሪዎች በእውቀትና በክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ።16
2.4.4. ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት ......................... 16
2.4.5. በመምህሩና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር። .................... 17
2.4.6. የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳድስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር። ........................................................................ 17
1. የቃላት ጫወታ ........................................................................ 17
1. የፕሮጀክት ክንዋኔ........................................................................ 18
2. ሚና ጫወታ........................................................................ 18
3. ለችግሮች መፍትሔ በማቅረብ መማር ........................................................................ 18
4. እርስ በእርስ በመደጋገፍ መማር ........................................................................ 19
5. ብጤን ማስተማር........................................................................ 19
6. ማነቃቃት ........................................................................ 19
2.4.7. የተለያዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን መገልገል ........................................ 20
2.4.8. ለተማሪዎች እውቅና መስጠትና መሸለም የሚሉ ናቸው። .............................. 20
2.5. ማበረታቻን ለቋንቋ መማር ፍላጎት ግብአት የማድረግ ጠቀሜታ............................ 20
2.6. ፍላጎት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትጋር ያለው ተዛምዶ.............................. 21
2.7. የፍላጎት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች ........................................................................ 21
2.7. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................................................ 23
ምዕራፍ ሦስት፤የጥናቱ ዘዴ እና ንድፍ ........................................................................ 27
3.1. የጥናቱ ንድፍ........................................................................ 27
3.2. የጥናቱ አካላይ........................................................................ 27
3.3. የጥናቱ የመረጃ ምንጭ ........................................................................ 28
3.4. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................................................ 28
3.4.1. የከተማ አስተዳደሩ ናሙና አመራረጥ ........................................................................ 28

3.4.2. የትምህርት ቤቱ ናሙና አመራረጥ ........ 29
3.4.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 29
3.4.4. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ንሞና አመራረጥ ........ 30
ሰንጠረዥ 1፡ የተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤ ........ 30
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 30
3.6. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 31
3.6.1. የማንበብ ክሂል ፈተና ........ 32
3.6.2. የጽሐፍ መጠይቅ ........ 32
3.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 34
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ ........ 36
4.1. የጥናቱ መረጃ ትንተና ........ 36
4.1.1. የጽሑፍ መጠይቅ ትንተና ........ 36
4.2. የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ትንተና ........ 46
4.2.1. የተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የንባብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ ........ 48
4.3. የውጤት ማብራሪያ ........ 50
ምዕራፍ አምስት፤የጥናቱ ማጠቃለያ እና አስተያየት ........ 52
5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ ........ 52
5.2. አስተያየት ........ 54
ዋቢ ጽሑፎች ........ 56
አባሪዎች ........ 60
አባሪ አንድ፡- ስለ ጽሑፍ መጠይቅ ........ 60
አባሪ ሁለት ........ 66
ስለ ማንበብ ክሂል ፈተና ........ 66
አባሪ ሦስት ........ 72
በኮድ ሽት የተመዘገበ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ........ 72
የጾታ ውክልና ........ 72
አባሪ አራት ........ 74
የንባብ ክሂል ውጤት ........ 74

አባሪ አምስት.......................................................................................................77
የማንበብ ፍላጎትና ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ፤.............................77
አባሪ ስድስት .......................................................................................................84
የተማሪዎች የማንበብ ልምድና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ተዛምዶ ስሌቶችን የሚያሳይ ማስረጃ፤..........................................................................................................84
አባሪ ሰባት ...........................................................................................................87
በትምህርት ቤቱ ለፈተና የተቀመጡ ተማሪዎች ...............................................................87
አባሪ ስምንት.......................................................................................................89
ከተተኳሪ ትምህርት ቤት መረጃ ስልመውሰዱ የተሰጠ ደብዳቤ.............................................89

# የሠንጠረዥ መውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፡- የተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤-------------30

ሰንጠረዥ ሁለት፡- የአጠቃላይ ማንበብን መማር ፍላጎትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች፤ ...37

ሰንጠረዥ ሶስት፡- የማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች፤ ................................40

ሰንጠረዥ አራት፡- የማንበብ ችሎታን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች፤ 43

ሰንጠረዥ አምስት፡- ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ክሂል በተግባር የማዋል ብቃት ለመገምገም ከተሰጠው የማንበብ ክሂል ፈተና ያገኙት ውጤት በመቶኛ፤ ...............................................47

ሰንጠረዥ ሰድት፡- የተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ የሚያሳይ መረጃ፤ ..........................................................................48

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት አላማ ያደረገው በዳውሮኛ ቋንቋ አፊቸውን የፈቱ በደ/ም/ኢ/ክ/መንግስት በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የውጤት ተዛምድን መፈተሽ ላይ ነው፡፡ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ወጤታማነት ለመፈተሽ በዚህ ጥናት የማንበብ ክሂል ፈተና ላይ የተመረኮዘ መረጃ ትንተና ላይ ያተኮረ በመሆኑ ጥናቱ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ የተሰበሰቡ የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ በተተኳሪ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል ስድስት ክፍሎች ያሉ ሲሆን በአጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል ካሉት 200 (ሁለት መቶ) ተማሪዎች በቀላል ዕጣ ናሙና ከእያንዳንዱ ክፍል 10(አሥር) ከስድስቱ ክፍል 60 ( ስልሳ ተማሪዎች ተመርጠው መረጃ እንድሰጡ ተደርገዋል፡፡ የፒርሰን የተዛምድ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ የተዛምዷቸው መጠን 0.199 ሆኗል፡፡ ይህም በተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ ምንባብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል 0.199% ያህል ተዛምዶ መኖሩን ያመለክታል፡፡ በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ያለው ተዛምዶ ጉልህነት ደረጃ 0.128 ሆነዋል፡፡ በተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና መካከል የታየው ተዛምዶ ከስህተት ነጻ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በተሠራው የአስተማማኝነት ግንኙነት መለኪያ ስሌት የ t-test ቀመር 2.349 ውጤት ተገኝቷል፡፡ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት እና የንባብ ፍላጎት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመለካት የምንባብ ፈተና ውጤት በመውሰድ የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የፒርሰን ተዛምድ ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ነው ጥናቱ የተካሄደው፡፡ በስታቲስቲካዊ መረጃው መሰረት የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ (የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት=0.199%), የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት = 0.128%) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ማለት የምንባብ ፈተና ውጤት (r = (0 .199%), p = (0.128%)፣ ይህም የንባብ ፈተና ውጤት እና በተማሪ ፍላጎት መካከል ጉልህነት ደረጃው በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መታየቱን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት በደቡብ ምዕራብ ክልል በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛና መሠናዶ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በተገኘው መረጃ መሠረት ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት ከንባብ ፈተና ውጤታቸው ጋር በጣም ዝቅተኛ ተዛምድ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ማንበብ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር እና ከመጻፍ አንደኛዉ ሲሆን ማንበብ በመማር የሚገኝ መልእክት መቀበያ ክሂል ነዉ፡፡

ማንበብን በተመለከተ የተለያየ ምሁራን የየራሳቸዉን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ እንደ David (2005፣1) በበኩላቸዉ ማንበብ ጸሀፊዉ በስራዉ ያሰፈረዉን ቁምነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነዉ፡፡ አንባቢዉ በንባብ ሂደት የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት፤ መረጃን ከዉስጥ ለይቶ ለማዉጣት፤ የጸሐፊዉን (የደራሲዉን) ሀሳብ ይመረምራል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ማንበብ ማለት መገመት፤መተንበይ የአእምሮን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ እና ፀሀፊው ያሰፈረውን ቁም ነገር መረዳትን የሚጠይቅ እንደሆነ መገንዘብ ነው፡፡

በተጨማሪም Sliberstein (1994፣ 12) የሰዉ ልጅ መረጃ ከሚያገኝባቸዉ መንገዶች አንዱ ማንበብ ነዉ፡፡ ነገር ግን የማንበብ ፍላጎት በጨመረ ቁጥር ለንባብ ክህል ያለው ቦታ ይሰፋል፣ ውጤቱም አውንታዊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ማንበብ የሰው ልጅ መረጃ የሚያገኝበት አንዱ እንደሆነና የማንበብ ፍላጎት ደግሞ የንባብ አድማስን የሚያሰፋ ንዑስ ክህል ነው ማለት ነው፡፡

ማንበብ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊና መሰረታዊ ከሆኑት ክሂልች ውስጥ አንዱ መሆኑን Lindsay and Knight (2006:70-71) ያመለክታሉ፡፡

የማንበብ ክሂል ቋንቋን በማስተማር ሂደት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የዚህ ክሂል በአግባቡ መዳበር ለሌሎች ክሂሎች ማደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ የተሻለ እና ጥሩ አንባቢ ለመሆን የዳበረ የንባብ ፍላጎት ያለው መሆን ያስፈልጋል፡፡ የዳበረ የሚባለው የንባብ ፍላጎት በተገቢው ተነሳሽነት አንብቦ መረዳትን የሚመለከት ነው (National Reading Panel 2000)፡፡ አንባቢ አንድን መልእክት ለመረዳት ምንባቡን ከውስትየመነጨ ፍላጎት ጋር ካላነበበ ምንባቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት መረዳት አይችልም ማለት ነው፡፡ የማንበብ ክሂል በውስጡ በርካታ ንዑሳን ክሂሎችን ይይዛል፡፡ ከነዚህም አንዱ የማንበብ ፍላጎት ነው፡፡
ከዝቅተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች ለንባብ ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው እንዲጨምር ደግሞ የተማሪዎችን ፍላጎት መለየት፣ የማስተማሪያ ዘዴን ማስተካከል፣ በማንበብ ትምህርት ተማሪዎች ማሳተፍ፣መምህሩ አንብቦ ካሰማቸው በኋላ እንድያነቡ ማድረግ፣ ጭምቅ ሀሳብ የያዙ ጽሁፎችን ማንበብ፣ የንባብ ፍላጎትን ለመጨመር የሚያስችሉ ሳቢ ጽሁፎችን አዘውትረው ማንበብ፣ ለረጅም ጊዜ የማንበብ ልምድን መኮትኮት ወይም መንከባከብ፣ ፍጥነትን በራስ ወስኖ ለማንበብ መዘጋጀትንና በንባብ ጊዜ ለሚነበበው ጽሁፍ ትኩረት የመስጠት ልምድን ማካበት ይኖርባቸዋል (Coonor et al., 2011)፡፡

የንባብ ፍላጎት ከንባብ በፊት ያለው የንባብ ስሜት እና ለንባብ የቀረበውን ጽሁፍ የምንገነዘብበት ሂደት ሲሆን አስቀድሞ በአንባቢው የተያዘውን እውቀትና የንባብ ልምድ መሰረት በማድረግ ከተነባቢው ጽሁፍ ጋር ንቁ ተራክቦ በማከናወን ትርጉም የማግኘት፣ የማብራራትና መረጃዎችን የመተንተን ክንዋኔ ነው፡፡ (Rasinski, 2012፣ Brown, 2011)፡፡ ባለንበት ዘመን አቀላጥፎ ማንበብና ማንበብ ፍላጎት የማይነጣጠሉና ተማሪዎች በሚኖሩበት በመረጃ የሚመራ አለም ውስጥ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዛቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡ (Coonor et al., 2011)፡፡ በዚሁ መሰረት የማንበብ መርሃ ግብሮች ተማሪዎቹ ለማንበብ ክሂል መሰረታዊ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ጠንቅቀው በመረዳት በህትመት ይሁን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የቀረቡ ጽሁፎችን አቀላጥፈው ማንበብና የንባብ ፍላጎታቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡ (Torgesen, 2012)፡፡ የማንበብ ብቃት ጥሩ አንባቢ ለመሆን ፍላጎት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

Jones (2008) እና ሌሎች እንደሚገልጹት ማንበብ ማለት ጽሑፍን ትርጉም የመፍጠርና የመጠቀም ልምድ ነው፡፡ ማንበብ አንድን ጽሑፍ መረዳት፣ መተርጎምና መልዕክትን በራስ አዕምሮ ማስረጽ ነው፡፡ ማንበብ ፊደሎችን፣ ምልክቶችን እና የመሳሰሉትን በተለይም በማየት ወይም በመንካት የመውሰድ ሂደት ነው፡፡

Willson (1971)፣ Hawit (1967)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ፍላጎት አንድን ነገር ለመተግበር ትኩረት የሚሰጥበት፣ እንዲሁም አንድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ውስጣዊ ግፊት፣ ዝንባሌና ስሜት ነው፡፡ አንድ ሰው አንድን ነገር ለማከናወን ትኩረት ሰጥቶና እራሱን እያዘጋጀ እያለ እንዲያከናውን በሚከለከልበት ጊዜ የብስጭት ስሜትን ሊፈጥር የሚችል ሃይል ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ወሳኝነት አለው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ማጥናት የተማሪዎችን ስነልቦናዊ ችግሮች በማቃለል ውጤታማ የሚሆኑበትን ሁኔታ ከማመቻቸት አንጻር ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርሱ ተላውጦዎች መካከል ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚኖር አመለካከትና ፍላጎት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ መሆኑን Gardner, et al., 2004) ያስረዳሉ፡፡

እንደ Tarin (1997) አገላለጽ "ፍላጎት ማለት አንድ ግለሰብ ስሜቱንና ዝንባላውን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም የአንድን ነገር ምንነት ለማወቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከት የሚገፋፋ ሃይል ነው፡፡ ይህም አንድን ነገር እንድንወደው ወይም እንድንጠላው የሚያደርግ ንቃተ ህሊናዊ ስሜት ነው በማለት ይገልጻል፡፡" በሌላ በኩል Skiner (1985)ን በመጠቀስ William (1990) እንደገለጹት "ፍላጎት የታቀደ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወነን ተግባር መውደድና አለመውደዳችንን የሚያመለክት ውስጣዊ ተነሳሽነትና ለተፈለገ ነገር ትኩረት እንድንሰጥ የሚያደርግ ግፊት፣ ዝንባሌና ስሜት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡"

ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል፡፡ ለመማር ፍላጎት የለሌው ከሆነ ትምህርቱን ፈጽሞ ሊማር አይችልም፤ ስለዚህ አንድን የትምህርት አይነት ለማስተማር በምንነሳበት ጊዜ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት የሚኖረው ፍላጎት አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ፍላጎት ካለው ትምህርቱን በሚገባ መከታተል ይችላል፡፡ ፍላጎት የለሌው ተማሪ ግን ትምህርቱን በተገቢው መንገድ መከታተል አይችልም (Bugals1971)፡፡

ፍላጎት የለሌውን ተማሪ እንዴት መለየት ይቻላል የሚለውን Guaraider (1985) ሲያስረዳ "ተማሪው የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ የማይከታተል ከሆነ፤ ትምህርቱ ሲሰጥ ከልብ የማያዳምጥና በትክክል መረዳት የማይችል ከሆነ፣ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪው የመማር ፍላጎት የለሌው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ምንም ፍላጎት የለሌው ከሆነ ደግሞ የመማር ማስተማሩ ተግባር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡" ስለዚህ ተማሪው ለሚሰጠው

ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ፍላጎት የለሌውን ተማሪ ማስተማርም በክፍል ውስጥ የለሌን ተማሪ እንደማስተማር ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪው ስለሚማረው ትምህርት ፍላጎት ከሌለው የሚሰጠውን ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመከታተል አይነሳሳም፤ ተነሳሽነት ደግሞ ከፍላጎት ጋር ጥብቅ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት መሰረት ምን ያህል ዕውቀት እንደቀሰሙና የተማሪዎች ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅና የታቀደው የተማሪዎች የባህሪ ለውጥ መምጣቱን ለማረጋገጥ በአጠቃላይ የትምህርቱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ለመፈተሽ የተለያዩ ፈተናዎች ይሰጣሉ፡፡ በዚህም የተማሪዎች የትምህርት ውጤት ምን ያህል እንደሆነ ይመዘናል (Brown 2003)፡፡ የቋንቋ ትምህርት ውጤት ከአንድ የቋንቋ ትምህርት የመማር ሂደትና ወቅት በኋላ በሚዘጋጅና ለተማሪዎች በሚሰጡ ተከታታይ ምዘናዎች አማካኝነት ሊለካ የሚችል መሆኑን Huges (2003) ያስረዳሉ፡፡

እንደ Scohon (1986) አገላለጽ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በከፍተኛ ፍላጎት እንዲማሩና ጉጉት እንዲያድርባቸው በቅድሚያ ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት ከሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ደግሞ ቀደም ብሎ ካሏቸው እውቀት ጋር አያይዘውና አዋህደው እንዲገነዘቡትና በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ካላቸው እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በቀላሉ ሊረዱትና ሊያውቁት ከመቻላቸውም በላይ የተማሩትን ለረዥም ጊዜ በአዕምሯቸው ይዘው እንዲቆዩ፣ በተማሩትና በሚያነቡት ሁሉ እንዲደሰቱ፤ ጥሩ ልምድና ተግባር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትና ውጤት ላይ ተፅዕኖ ከማድረስ አንጻር በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጪ የሚኖሩ የተጽዕኖ አከፋፈሎች እንዳሉ የሚያስረዳ ምሁራን አለ፡፡ ውስጣዊ የሚባሉት ተማሪው በሚማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ሲሆኑ የትምህርት ቤቱ አካባቢ፣ የመምህራን ማንነት፣ የትምህርት መሳሪያዎች ሁኔታ፣ የመመዘኛ መስፈርቶች፣ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ፣ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ውጫዊ የሚባሉት ደግሞ ከትምህርት ቤት ውጪ ሊኖሩ የሚችሉ የቤተሰብና የማህበረሰብ ባህላዊ ዳራዎች፣ የተለያዩ እምነቶችና አጠቃላይ ተማሪው የሚኖርበት ህብረተሰብ አስተሳሰቡና ልማድ የሚሉ ሲሆኑ፤ እነኚህ ውጫዊ የተባሉት

ሁኔታዎች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትና በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም፡፡
ከላይ በተገለጹት ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ፍላጎት ማለት በአንድ ነገር ለመሳብ ወይም ለመገፋት ምክንያት የሚሆን ውስጣዊ ስሜት ሲሆን አንድን ነገር ከመውደድና ከመጥላት ጋር በተያያዘ ለመምረጥ ወይም ላለመምረጥ ምክንያት ሊሆን የሚችል ህሊናዊ ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ፍላጎት የትምህርትን የመጨረሻ ግብ ለማሳካት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉትና የሚሰጠውን ተግባር በአግባቡ እንዲያከናውኑ እንዲሁም ፍላጎታቸውን ማነሳሳት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ፍላጎት ከሌለ የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ማካሄድም ሆነ በስርዓተ ትምህርቱ የተቀረጸውን ግብ ማሳካት አዳጋች ያደርገዋል፡፡
ስለሆነም ይህ ጥናት በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህልን ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶን የሚመረምር ይሆናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ሂደቱ ውስጥ የሚኖረው ፍላጎት በሚያስመዘግበው የቋንቋ ትምህርት ውጤት፣ የመማር ተግባራቱ፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ልመለከታቸውና ሊያሻሽላቸው በሚችላቸው ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን የመማር ፍላጎትና በትምህርቱ ውጤታማ መሆን አለመሆን ጋር በተገናኘ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ተመራማሪዎች፣ በተለያዩ አካባቢዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡
ከእነዚህ መካከልም Sufi (2009)፡፡ በተማሪዎች ፍላጎትና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? በሚል በጃካርታ ሸሪፍ እስላሚክ ስቴት ዩኒቨርስቲ ባካሄዱት ጥናት በተማሪዎች ፍላጎትና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ጉልህ ተዛምዶ ያለ መሆኑን አሳይተዋል፡፡ በዚህም እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማር ፍላጎት ያሏቸው ተማሪዎች በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ የሚያደርስበት መሆኑንና ፍላጎትና ውጤታማነት የርስበርስ ቁርኙት እንዳሏቸው፤ ዝቅተኛ ፍላጎት ዝቅተኛ ውጤትን፤ ዝቅተኛ ውጤትም መልሶ ዝቅተኛ ፍላጎትን እንሚያስከትል አመላክተዋል፡፡

Coler and Jergun.(2001) በተማሪዎች ፍላጎትና በሂሳብ ትምህርት ውጤታማነት መካከል ተዛምዶ ይኖር ይሆን? በሚል በጀርመን ሚችጋን ዩኒቨርሲቲ ባካሄዱት ጥናት በፍላጎትና በውጤታማነት መካከል ጉልህ ዝምድና (ተጽዕኖ) የለም፤ ነገር ግን ፍላጎት በትምህርት ዓይነት (በኮርስ ምርጫ) ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አሳይተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ውጤታማነት በፍላጎት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሲሆን ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ የሚኖራቸው ፍላጎት ከደካማ ተማሪዎች የተሻለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተመሳሳይም Alfayzah, Noro and Camnun (2020) በተማሪዎች ፍላጎትና አጫጭር ምንባቦችን አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር በኢስላም ኒጅሪይ የአልሁዲን ማካሳር ዩኒቨርሲቲ በጎዋ ሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በካሄዱት ምርምር ዝቅተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን አሳይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ጥናቶች ስንመለከታቸው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ፍላጎትና በትምህርት ውጤታማነት ላይ አተኩረው የተካሄደ ቢሆንም ሁሉንም በጋራ የሚያስማሙ ግኝቶች አለ ማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ከዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ስኬትን በተመለከተ አሁንም በፍላጎትና በውጤት መካከል ተዛምዶ ላይ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህም አጥኚው በዚህ ርዕስ ጥናት እንዲያካሂድ ያነሳሳበት ምክንያት ከዚህ እንደሚከተሉት የቀረቡት ናቸው፡፡

አጥኚው ካለው የማስተማር ተሞክሮ መረዳት እንደቻለው ጥናቱ በሚካሄደበት አካባቢ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ውጤት እንዲሁም በንባብ ክህል ፍላጎት ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ለውጤታቸው መቀነስ አንደኛው ምክንያት ፍላጎት ይሆን? የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ ያደረገ በመሆኑ፣ የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ከውጤት ጋር ያላቸለው ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ፣ በተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ የማንበብ ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይሆን የሚለው ሁኔታም ለዚህ ጥናት መካሄድ አነሳሽ ምክንያት መሆኑ፣ ከዚህ በፊት በዚህ ርዕስ በተለያዩ በውስትና በውጭ ሀገራት የተሠሩ ጥናቶች ቢኖሩትም በዳውሮኛ አፋቸውን በፈቱ ተማሪዎች ላይ ያልተሠራ በመሆኑ እና ማንበብ የተማሪዎችን የማወቅ ፍላጎት፣ የቃላት እውቀት፣ የመጻፍ ተነሳሽነት ስለሚያሳድግ አጥኚው ጥናቱን እንዲያጠና አነሳስተዋል፡፡

### 1.3. የጥናቱ መላምቶች

ለጥናቱ የሚከተሉት መላምቶች ተነድፈዋል፡፡

ሀ. በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል አዎንታዊ ዝምድና አለ፡፡

ለ. በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል አሉታዊ ዝምድና አለ፡፡

ሐ. አልቦ መላምት፣ በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል ምንም ዓይነት ዝምድና የለውም፡፡

### 1.4. የጥናቱ ዓላማ

በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን መማር ፍላጎት ከማንበብ ክሂል ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶን መፈተሽ ነው፡፡

#### 1.4.1. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

ለዚህ ትናታዊ ጽሑፍ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

ሀ. በተተኳሪው ቋንቋ የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ፣

ለ. የተማሪዎች የማንባብ ፍላጎት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶን መፈተሽ እና ዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ መመርመር ናቸው፡፡

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን ከማስቀመጥ አንጻር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡
ሀ. ተማሪዎቹ በጥናቱ ውጤት ላይ ተመርኩዘው በአማርኛ ትምህርት ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል የፍላጎት መጠን መስመር ለመያዝ ጥረት እንዲያደርጉ ሊያነሳሳ ይችላል፡፡

ለ. በሁለተኛ (አማርኛ) ቋንቋ ትምህርት መማር ላይ አነስተኛ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊና ጠቃሚ የማነቃቂያ እገዛ ለመስጠት የበለጠ ፍላጎት እንዲኖራቸው ሊረዳ ይችላል፡፡

ሐ. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት በፍላጎትና በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ስለሚኖረው ተዛምዶ ለማወቅና ከዚህም ተጠቃሚ ለመሆን ለሚፈልጉ ተማሪዎች መምህራንና ተመራማሪዎች ጠቃሚ መረጃን ሊሰጥ ይችላል፡፡

መ. የአማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚያስተምሩ መምህራን በጥናቱ ውጤት መሰረት ፍላጎት በፆታና በዕድሜ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ተገንዝበው የመማር ማስተማሩን ሂደት በዚያው ላይ ተመስርተው ለማከናወን የሚያስችል መረጃን ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሠ.ለስርዓተ-ትምህርት ቀራጮችና ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ከስራቸው በፊት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎትን ከግምት እንዲያስገቡ መረጃ በመስጠት ሊያግዝ ይችላል፡፡

ረ. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እና በፍላጎት እና ውጤት ተዛምዶ ዙሪያ የሚካሄደው ጥናት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ወደፊት ይህንን ርዕስ አስመልክቶ ለሚደረጉ ምርምሮች መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማለትም ጭጮ እና ደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡
ይህ ጥናት ከፍላጎት ባሻገር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ሌሎች ተላውጦዎችን የመፈተሽ ትኩረት የለውም፡፡ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ በ2016 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በዳውሮኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፍዎች ሆነዋል፡፡
ጥናቱ ከይዘት አንጻር የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል የመማር ፍላጎት ከማንበብ ክሂል ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶን ቃኝተዋል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ

በዚህ ጥናት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ትምህርት ፍላጎት፣ ተዛምዶና ውጤት የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ሲሆኑ ተግባራዊ ብያኔያቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሁለተኛ ቋንቋ፡-** ተማሪው ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ቀጥሎ የሚለምደውና ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ውጪ ከመማርም ሆነ ተግባቦት ለማድረግ የሚጠቀምበት ቋንቋ ነው፡፡

**ፍላጎት፡-** አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የተማሪዎች ስሜት፣ ግፊት፣ ዝንባሌና ጥረት ነው፡፡

**ውጤት፡-** ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና የሚያገኙት ግኝት ነው፡፡

**የማንበብ ፍላጎትና ውጤት ተዛምዶ፡-** አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በሚኖራቸው የማንበብ ፍላጎትና በሚያስመዘግቡት የፈተና ውጤት መካከል የሚኖር አዎንታዊ ወይም አለታዊ የተዛምዶ ውጤት ግንኙነትን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል በጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን መቅረጽና የጥናቱ አቅጣጫ ለማሳየት የሚረዱ አስፈላጊ የሆኑ ንድፈ ሃሳቦች የሚቀርብበት ነው፡፡ ይህ ክፍል ስለ አማርኛ ቋንቋ ንባብ ክሂል መማር፣ ለተማሪዎች ያላቸው ፍላጎትና ውጤት ተዛምዶ የተለያዩ ምሁራን ያስቀመጡትን ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦችን የሚዳስስበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1. የፍላጎት ምንነትና ጽንሰ ኃሳባዊ መሰረቶች

የተማሪዎች ፍላጎት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት የሚያበረታታና በተለያዩ ስልቶች፣ ዘዴዎች ብልሃቶችና ሞደሎች እንዲሁም በቀደሙ የመማር ልምዶቻቸው ላይ ተደግፎ የሚቀርበውን ስርአተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት እንዲወዱት አልያም እንዲጠሉት የማድረግ አቅምን የሚወስን፣ ስነ-ትምህርታዊ አቀራረቦችን፣ ይዘቶችንና ጽንሰ ሀሳቦችን በመረዳት ረገድ ቁልፍ ሚና ያለው ነው፡፡ (McCarthy, 2014)፡፡

በReid (1995) እንደተገለጸው የመማር ፍላጎት /ምርጫ/ ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት አቀራረብ ላይ የተያያዘ ባህሪና አመለካከት ሲሆን ይህም በአንድ በተወሰነ አውድ የሚቀርበውን ይዘት የመረዳት ተነሳሽነታቸውን ብቻ ሳይሆን ውጤታማነታቸውን ለማመቻቸት ወሳኝ መነሻ ነው፡፡

የመማር ፍላጎት ጽንሰ ሀሳብ በተማሪዎች የእለት ተእለት የመማር ክንዋኔ ውስጥ ቁልፍ ድርሻ አለው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከሚማሩት ትምህርት ጋር በተያያዘ መረጃዎችን የሚቀበሉባቸው የየራሳቸው ልምዶችና ፍላጎቶች ይዘው ስለሚገኙ ነው፡፡ ባለንበት ዘመን የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎች ትምህርት ለመቀበል የሚጠቀሙባቸውን ግላዊ ስልቶችና ብልሃቶች በመመርመር በመማር ሂደት ተጨባጭ ለውጥ እንዲያሳዩና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ በሰፍው ልጠቅሟቸው የሚችሉ ተግባራትን የማከናወን ብቃት እንዲቀዳጁ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ስነዘዴዎች፣ ስልቶችና ብልሃቶችን በመቀየስ ረገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ (Willemse, Lunenberg and Korthagen 2005)፡፡

የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማወቅ የመጀመሪያው ተግባር ተማሪዎቹ ምን ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉና ምን መስራት እንደሚፈልጉ ማወቅ ነው፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት አሰሳ ከተማሪዎች የቀደሙ ልምዶች ዳሰሳ መነሻ ማድረግ ይቻላል፡፡ ወይም የተለያዩ የፍላጎት አማራጮችን አቅርቦ ተማሪዎችን በማስወሰን ፍላጎቶቻቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡ በርከት ያሉ ተማሪዎች ተመሳሳይ የእሾት ዳራዎችን ሊጋሩ ይችላሉ፡፡ ይህም በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ የጋራ ፍላጎት መኖርን ያመለክታል፡፡ የጋራ ፍላጎት መኖር የጋራ የመማር ዝግጁነት ወይም ልምድ የመቀበል ተነሳሽነት መኖሩን ገላጭ ነው፡፡

### 2.1.2. የፍላጎት ተኮር ትምህርት አስፈላጊነት

ፍላጎት ተኮር ትምህርት የትምህርቱን አቀራረብ ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ የሚረዳ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት በተማሪዎቹ ውሳኔ ሰጪነት ሚና ለማስመርኮዝ ጠቀሜታ ያለው አዲስ አተያይ ሲሆን ምን እንደምናስተምር፣ ምን ያህል እንደምናስተምር፣ ለምን ያህል ጊዜ ትምህርቱ መሰጠት እንዳለበት ለመወሰን የሚረዳ በመሆኑ ተማሪዎች በመማር ሂደቱ ተደሳችነትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የበኩሉ ድርሻ ከፍ ያለ ነው፡፡ በፍላጎት ተኮር ትምህርት ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ስለሚሆኑ የሚቀርብላቸውን ይዘት በራሳቸው ይቆጣጠሩ ዘንድ ተበረታችነት ያሳያል፤ የሚሰጧቸውን ተግባራትና ክንዋኔዎች በተራክቦ ያዳብራል፤ ስለሚማሩት ይዘት በተሻለ ኃላፍነት መንፈስ ስለሚያከናውኑ በተሻለ ቅልጥፍና ይሸፍኑታል ተብሎ ይታመናል (Renninger, Hidi and Krapp, 2012)፡፡

ፍላጎት ተኮር የመማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን እሾቶች ማእከል አድርጎ እንደመቅረቡ መጠን ተማሪዎቹ ወደ መማሪያ ክፍል ይዘዋቸው የሚመጧቸውን ልምዶች፣ አስተሳሰቦችና አሰራሮች በመጋራት የሚማሩትን ይዘት በፍጥነት በመሸፈን ወደ አዲስ ይዘት እንዲሸጋገሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በትምህርቱ ይዘት ውስጥ አስቀድሞ የሚያውቋቸውን ጉዳዮች ከማያውቋቸው አዳድስ ይዘቶች የመለየት እድል ስለሚያገኙ በአዳድስ ጽንሰ ሀሳቦችና ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ጉልህ አጽንኦት በማድረግ ትኩረቶቻቸውን አሰባስበው እንዲማሩ ለማድረግ ይረዳል (Hoffmann, 2002)፡፡

### 2.1.3. ፍላጎት ተኮር ትምህርትን ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማቅረብ ጠቀሜታ

ፍላጎት ተማሪዎች በጽናት የሚቆሙለት ባህሪያቸው በመሆኑ መምህራን ፍላጎታቸው ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመምረጥ ወደ ክፍል ይዘው መምጣት ትምህርቱን ተግባራዊና ተማሪዎቹን ውጤታማ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተመሳሳይ

መልኩ Walkington & Sherman (2013)ም እንደገለጹት፣ መምህራን ተነሳሽ መሆን ያለባቸው ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተዛመደ ማራኪ ርእሶችን በመምረጥ የመማሪያ አውዱን ለተማሪዎቹ አስደሳች በማድረግ፣ የመማር ተግባራቱንም ተወዳጅ ማድረግ ይኖርባቸዋል ባይ ናቸው። እንደ Walkington & Sherman (2013) እምነት ፍላጎት ተኮር ቋንቋ ማስተማር (IBLT) የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው።

በዚሁ መሰረት እንደ Hidi and Harackiewicz (2008) አገላለጽ፣ ትምህርት ቤቶችና መምህራን የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሳድግ በሚያግዙና ውጤታማነታቸውን በሚያሻሽሉ ስልቶችና ብልሃቶች አስሶ በማቅረብ ላይ ብርቱ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል። በእርግጥ ተግባቦታዊና አሳታፊ የሆኑ ተግባራት ለግልና ለቡድን ውጤታማነት ተመራጭ እየሆኑ መጥተዋል። እንደ Walkington & Sherman (2013) አገላለጽ፣ በፍላጎት ዙሪያ የሚደረግ አጽንኦት አዋጭ የሆኑ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መጠቀም፣ ከመረጃዎች በመነሳት መወሰንን የሚጠይቅ ነው። ይህም ተማሪዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ልምድና የተማሩትን መረጃ ለተራዘመ ጊዜ አስታውሶ የመጠቀም ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ይህን ፍላጎት ተኮር የመማር እሳቤ ከትምህርት መጀመሪያ እድሜ ጋር አዛምዶ ማቅረብ ተማሪዎች ከጅምሩ ተሞክሮውን እየተገነዘቡ፣ አብዛኛውን የመማር ጊዜያቸውን በፍላጎት ላይ ተመርኩዘው በሚቀርቡ ልምምዶች ውስጥ እየተሳተፈ እንዲዘልቁ ስለሚያደርግ እያደጉ ሲሄድ ስለራሳቸው መማር የበለጠ የኃላፍነት ስሜት ይሰማቸዋል። በትምህርቱ ሂደት ተደሳች ስለሚሆኑ ውጤታማም ያደርጋቸዋል ተብሎም ይታመናል። (McCarthy, 2014)።

## 2.2. የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጠበቅ የሚረዳ ብልሃቶች

ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ኖሯቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ቀዳሚው ተግባር በመማር አውዶች የተሻለ የሚመሰጡባቸውንና የሚደሰቱባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማወቅ እነዚህን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ማድረግ ነው። ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ይዘት ከፍላጎታቸው ጋር እንዲስማማ ለማድረግ በመማር ሂደት አብዝተው የሚያተኩሩባቸውንና ለመስራት የሚወዷቸውን ጉዳዮች በማሰስ እነዚህን የመማሪያ ቴክኒኮች የትምህርቱ እቅድ አካል በማድረግ ፍላጎታቸውን መያዝ እንደሚቻል Willemse, Lunenberg & Korthagen, (2005) ይገልጻሉ። በመማር ማስተማሩ አውድ ተማሪዎች ጥሩ ፍላጎት እንዲያሳድጉ ከማድረግ አንጻር የተማሪዎችን የመማር ችግሮች፣ የተነሳሽነት ጉድለቶች፣ ከቤተሰብ ጋር የተያያዙ አለመመቻቸቶች ለይቶ በማወቅ ለማቃለል መሞከር

አስፈላጊ ነው። በመማር ማስተማሩ አውድ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማምጣት Willemse, Lunenberg & Korthagen, (2005) በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማትኮር እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ፡-

በተቻለ መጠን የመማር ማስተማሩን ሂደት ተማሪዎቹ እንዲቆጣጠሩት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ላይ የተመሰረተ የማንበብ አውድ መፍጠር ለማንበብ ፈላጎትና ግፊት እንዲኖራቸው አጋዥ ነው።

በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳትፍ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጠቀሜታ አለው።

በጨዋታዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት (Game-based learning) እንደ አንድ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በመያዝ የትምህርት ይዘትን ለማቅረብ በሚረዳ መሳሪያነቱ በእጅጉ ታዋቂ የፍላጎት መንከባከቢያ ብልሃት ነው።

ተማሪዎች ወደ ክፍል ይዘው የሚመጧቸው ተፈጥሯዊ የሆኑ የመማር ስልቶች (learning styles) እንዳላቸው በርካታ ጥናቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ እነዚህን ለይተው በማወቅ ተማሪዎች እንዲተቀሙ ዕድል መስጠት ነው።

መምህሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁሉም የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ጠብቆ ወይም ተንከባክቦ ለመዝለቅ እና ተማሪዎች ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ ማገዝ ይኖርበታል።

## 2.3. የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ግንኙነት/ተዛምዶ

Linnenbrink and Pintrich (2008) እንደገለጹት፣ የመማር ፍላጎት ሲነሳ አብሮ በብዙዎች አእምሮ ታሳቢ የሚሆነው ጉዳይ ከሚማሩት የትምህርት አይነት ጋር ተያይዞ የሚገኘው የመማር ውጤታማነት (achievement) ነው።

ይህ የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ሊጤን የሚገባው ከተማሪው የመማር ፍላጎት በጥሩ ሁኔታ ዳብሮ መገኘት ጋር መሆን ይኖርበታል።

የፍላጎትና ውጤታማነት ትስስር በተበጁ የውጤት መለኪያ መሳሪያዎች በመደገፍ ተማሪው ባሳየው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ላይ ብቻ የሚመረኮዝ ከሆነ ወደ ትክክለኛ የፍላጎት ድምዳሜ ልያደርስ ይችላል ይላል። (Hidi, 2013)።

የፍላጎት ጽንሰሀሳብ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ለአንድ የተወሰነ የትምህርት አይነት /ይዘት/ ያላቸውን የመውደድ ስሜት በመማር ተራክቦ (affective reaction) የሚገልጹበት ስነልቦናዊ አቋም ነው። (Barron & Harackiewicz, 2000)። እንደ ምሁራኑ ገለጻ ከሆነ

የመማር ፍላጎት እና ውጤታማነት ተዛምዶ ተማሪው በትምህርት ሂደቱ ባሳየው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ላይ የሚመረኮዝ የፍላጎት ድምዳሜ ነው፡፡

## 2.4. በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን በተማሪዎቹ ዘንድ ለማስረጽ የቋንቋ መምህራን ሚና

ለሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል የመምህሩ የአመራር ሚና ለተማሪዎች ፍላጎት መንስራራት አይነተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መምህሩ ያልተቋረጠ የድጋፍ ሚና የመማር ማስተማሩን ሂደት በፍላጎት እንዲታገዝና ይበልጥ አነቃቂ እንዲሆን ያግዛል፡፡ በፍላጎት ማጠናከሪያ ስልቶች በሚገባ የተካኑ የቋንቋ መምህራን ትኩረት ማድረግ የሚገባቸው የተማሪዎችን ፍላጎቶች ከመንከባከብ ባሻገር ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን በፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲማሩ አስፈላጊውን ጥረትና እገዛ ሁሉ ማድረግ ነው፡፡ (Wright, 2016፤ 42)፡፡ ለዚህም የመምህሩ የአመራር ሚና ከዚህ በታች በተጠቀሱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አጽንኦት ማድረጉ ለውጤታማነት ይረዳል፡፡ (Huang, 2011፤ 50)፡፡

### 2.4.1. ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር አስተሳሰብን በፍላጎት እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡

ምንም እንኳን ተማሪዎች ምሉእ የሆነ አትኩሮት ያላቸው ሆነው ቢገኙም ለረጅም ጊዜ በተግባራት ላይ አትኩረው የመስራት ተመሳሳይ ፍላጎት ይዘው ላይገኙ ይችላሉ፡፡ የቋንቋ መምህሩ ይህን በመገንዘብ ተማሪዎቹ የትምህርቱን አላማ፣ ለተማሪዎቹ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ፣ ተግባሩን የሚያከናውኑበትን ብልሃትና ከእያንዳንዳቸው የሚጠበቁ የተሳትፎ ግንኙነቶች አስቀድሞ በመግለጽ በተማሪዎቹ ዘንድ አስፈላጊውን ቅድመ ግንዛቤ በመፍጠር ፍላጎታቸውን ቢያነሳሳ ጥሩ ተሳትፎና ውጤታማ ተራክቦ ለማካሄድ ያስችላል (Huang, 2011)፡፡

### 2.4.2. ተማሪዎች በእውቀትና ክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎት በውስጣቸው ማስረጽ

John Locke በአንድ ወቅት እንደገለጸው፣ ‹‹ፍላጎት በለሌበት ጠንካራ ተግባር ሊኖር ከቶ አይችልም፡፡›› በዚሁ መሰረት ተማሪዎች ጊዜና ነባር ልምዶቻቸውን በአግባቡ በመጠቀም ራሳቸውን ችለው እንዲማሩ፣ ፈጠራዊ በሆነ መንገድ ችግሮችን እንዲፈቱ፣ የተበረታታ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የገሃዱ አለም መስተጋብራዊ ልምምዶችን በተነሳሽነት እንዲያከናውኑ ማበረታታትና ማትጋት አስፈላጊ ይሆናል (Gu, 2010)፡፡

### 2.4.3. ተማሪዎች በእውቀትና በክህሎት ሊደርሱበት የሚገባ ፍላጎትን በውስጣቸው ማስረጽ፡፡

የሚደረስባቸው እውነተኛ /ተጨባጭ/ የቋንቋ መማር ግቦችን ማስቀመጥና እነዚህን ትምህርታዊ ግቦች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመጨበጥ የሚደረግ ትምህርታዊ እንቅስቃሴ በተማሪዎች አስተሳሰብ ውስጥ የመማር ፍላጎትን ለማስረጽ ቁልፍ ጠቀሜታ አለው፡፡ ተማሪዎች ግቦቻቸውን የመድረሻ ነጥባቸው ማገናዘቢያ አድርገው በትኩረት በመመልከት ከተቀመጡት ግቦች ትይዩ ትምህርታዊ እርምጃ እንዲያሳዩ ውስጣዊ ግፋትና ተነሳሽነት ይፈጥርላቸዋል (Gu, 2010)፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን በቋንቋ ትምህርቱ መጀመሪያ ተጨባጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትምህርታዊ ግቦችን በመርሐ-ትምህርቱና በተማሪዎቹ የቋንቋ መማር ፍላጎቶች ላይ ተመርኩዞ ተማሪዎቹን ባሳተፈ መልኩ ቢቀርጹ ተማሪዎቹ የስኬት አስተሳሰብ እንዲይዙ፣ አስቀድሞ ከሚሰሩት የተሻለ እንዲሰሩና በመማር ማስተማሩ ሂደትም የበለጠ ተሳታፉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታሰባል (Huang, 2011፣ (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡

### 2.4.4. ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት እንዲገነቡ ማበረታታት

በብዙ የዘርፉ ምሁራን ዘንድ የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ በራስ መተማመን ለከፍተኛ ውጤታማነት እንደ ድልድይ የሚያገለግል መሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎች በራስ የመተማመን አስተሳሰብ ይዘው የሚገኙ ከሆነ ውጤታማነት /ስኬታማነት/ አይቀሬ መዳረሻቸው ይሆናል፡፡ ይሁንና ቤት በአንድ ጊዜ ተግንብቶ እንደማይጠናቀቅ ሁሉ በራስ የመተማመን አስተሳሰብም በአንድ የሚጨበጥ ጉዳይ አይደለም፡፡ በራስ መተማመን በአጭር ጊዜ የሚደረስበት ግብ ባይሆንም ለተማሪዎች የመማር ሰብእና መገንባት እጅግ አስፈላጊ ግብአት ነው (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡ ከሁሉም በፉት የቋንቋ መምህራን ራሳቸው ለተማሪዎች መልካም ምሳሌ /ሞዴል/ በመሆን በራስ የመተማመን ሰብእናን እንዲላበሱ አነሳሽ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቋንቋ መምህራኑ ስኬታማ ለመሆን የሚያስችሉ እድሎችና አማራጮችን እንዲለማመዱ ለማድረግ የሚያስችል የግንኙነት አውዶችን በመተግበር ያሏቸውን ችሎታዎች እንዲያሳዩ ፍላጎታቸውን ማንሰራራት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም መምህራን ለተማሪዎቻቸው በልዩ ልዩ ችሎታዎች እውቅና መስጠትና መሸለም እንድ አንዴ የማበረታቻ ስልትም፣ ጠቃሚ የሆነ በራስ መተማመን የመገንቢያ መንገድም ነው (Wright, 2016)፡፡

### 2.4.5. በመምህሩና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር።

ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ላይ ከፍ ያለ ፍላጎት የሚያሳድሩት ከመምህሩ ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ሲኖራቸው ነው። የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከመምህሩ ጋር ባላቸው ግንኙነት ጤናማነት ላይ የተመሰረተ ነው። ተማሪዎች መምህራቸውን የሚያደንቁ ከሆነ የመምህሩን ትምህርት ይወደታል፤ በዚህ የተነሳ የሚቀርቡትን ይዘቶች በመማር ፍላጎት ታግዘው ይቀስማሉ። በመሆኑም መምህራን በተቻሏቸው አቅም ከተማሪዎች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነትን በመጠበቅ፣ በመተማመን፣ በመከባበር፣ በመዋደድ የመማሪያ አውድን ለቋንቋ ትምህርት ፍላጎት መንከባከቢያነት ማዋል ይኖርባቸዋል (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)።

### 2.4.6. የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማንሰራራት የሚረዱ አዳድስ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መተግበር።

በተወሰነ መልኩ በእርግጥ አብዛኛዎቹ ልማዳዊ የማስተማሪያ ሞዴሎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመንከባከብና ለማጎልበት ጠቀሜታቸው ያነሰ መሆኑን በርካታ ጥናቶች ያመለክታል (Gu, 2010፣ Jacobs & Eccles, 2010፣ Barron & Harackiewicz, 2000)። ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው በአብዛኛው ንቁ አድማጭ በመሆን እንደ ባዶ ጠርሙስ የሚንቆረቆርላቸውን ብቻ መቀበል ጠቀሜታውና ውጤታማነቱ ያነሰና ኢ-ንቁ የሚያደርጋቸው ነው። በመሆኑም ተመራማሪዎች የተለያዩ አዳድስ /ምትክ/ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ብልሃቶችን በመቀየስ የመማር ሂደትን አሳታፊና ተራክቦአዊ ለማድረግ ሞክረዋል (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)። አንድ ማህበረሰብ በማያቋርጥ የእድገት ሂደት በመለወጥ ላይ እንደመገኘቱ ሁሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችም ከዚሁ ለውጥ ጋር ተያይዘው በመሻሻል ላይ ይገኛል። በዚህም የተነሳ የቋንቋ መምህራን እነዚህን አዳድስ የቋንቋ መማሪያ ሞዴሎች በመተግበር የቋንቋ መማሪያ አውድን አስደሳችና መስህባዊ አድርገው ለተማሪዎቻቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል (Gu, 2010፣ Jacobs & Eccles, 2010፣ Barron & Harackiewicz, 2000)። የተለያዩ በቋንቋ መማሪያ አውድ ፍላጎትን ከፍ በማድረግ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ ጠቀሜታ ያላቸው ብልሃቶች በዘርፉ ምሁራን ቀርበዋል። ከእነዚህም መካከል በመደጋገፍ መማር፣ ብጤን ማስተማር እና ማነቃቃት የመሳሰሉት ናሙና ብልሃቶች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት ባላቸው ቀጥተኛ ድጋፍ እዚህ መጥቀስ አስፈልጓል።

#### 1. የቃላት ጫወታ

የቃላት ጫወታ በማስመሰል ላይ ተመስርቶ ፍላጎትን ከፍ ለማድረግ የሚቀርብ መማሪያ ብልሃት ነው። የጫዋታ ህግጋትና ውሳኔዎችን አስቀድሞ በማብራራት የጨዋታውን አሸናፊ

መለያ ነጥቦችን በግልጽ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በሚገባ የተደራጀ የቃላት ጫዋታ ተማሪዎች ረቂቅ ሀሳቦችን በቀለሉና በፍጥነት በመተግበር የንግግር ክሂል፣ ውሳኔ የመስጠት እና አስመስሎ ሚና የመጫወት ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

### 1. የፕሮጀክት ክንዋኔ

የፕሮጀክት ክንዋኔ ከህይወት ተሞክሮ መማርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ግላዊና ማህበራዊ ችግሮችን ማቃለል ላይ ያተኮረ የቡድን ሥራ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያልቀረቡ አካባቢያዊ የአኗኗር ገጽታዎችን ናሙና ወስዶ ለመፈተሽ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በዚህ ብልሃት ሊካተቱ የሚችሉ ፍላጎት አነሳሽ ተግባራትን መምህሩ መርጦ በማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲመረምሩ በማድረግ ተማሪዎች በታቀደ መልኩ በጥንቃቄ እንዲሰሩና ውጤቱን እንዲያቀርቡ ሊያደርጋቸው፤ የተሻለ የሰሩ ቡድኖችን በመምረጥ ሊያበረታታ ወይም እውቅና ሊሰጥ ይችላል (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

### 2. ሚና ጫወታ

ሚና ጫወታ አንደ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመያዝ የሚረዳ ማስተማሪያ ብልሃት ሲሆን ትኩረቱ ተማሪዎች አስመስለው እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቃለመጠይቅ አቅራቢና ቃለመጠይቅ ሰጪ፣ ወላጆችና ልጆች፣ ሐኪም እና በሽተኛ፣ አለቃና ሰራተኛ፣ ወዘተ ሚናዎችን ተማሪዎች አስመስለው ሊተውኑ ይችላል፡፡ ይህ ዘዴ በአብዛኛው የትምህርቱን ይዘት ተውኔታዊ ተግባቦታዊ አድርጎ ለማቅረብ አጋዥነቱ ከፍ ያለ ሲሆን የትምህርቱን ሂደትም እየተዝናኑ እንዲማማሩበት ለማድረግም ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በአብዛኛው የእውኑ አለም ግልባጭ የሆኑ ድርጊቶችና ግንኙነቶች ተሰናድተው የሚቀርቡበት እድል ሰፊ ነው፤ ይህም ትምህርቱን ትውስታ ፈጣሪ ወይም አይረሴና አዝናኝ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ሆኖም በሚና ጫዋታ የሚቀርበው ትምህርት በመጫወት ለመማር እንጂ ጫዋታ ብቻ ላይ ያተኮረ እንዳይሆን መምህሩ በቅድመ-ዝግጅት ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል (MOE, 2004፣ ICDR, 2009)፡፡

### 3. ለችግሮች መፍትሔ በማቅረብ መማር

ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ብልሃት የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ከሚረዳ ብልሃቶች አንዱ ነው፡፡ ICDR (2009) እንደቀረበው፣ በችግር ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ክፍተትን ለመሙላት የሚቀርብ ብሎም ውጤቶችንና የመፍትሄ አማራጮችን ለመጠቆም የሚረዳ ክንውን ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ውጤቱ ወይም መፍትሄው የችግሩን ክፍተት መሙላትን ታሳቢ አድርጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ሂደት ‹‹ዘዴ-ውጤት ትንተና›› (means-ends analysis) ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህም የተነሳ ችግር ፈቺ ፍላጎት ተኮር ብልሃት ተማሪዎቹ በሚገኙበት የክፍል ደረጃ ባላቸው የእውቀት ክፍተት ላይ ተመስርተው የሚፈለገውን አዲስ እውቀትና ክህሎት ለመጨበጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል (ICDR, 2009)፡፡

### 4. እርስ በእርስ በመደጋገፍ መማር

በMOE (2004፣ 94) እንደተገለጸው፣ በመደጋገፍ መማር ተማሪዎች ትንንሽ ቡድኖችን መስርተው እርስ በርስ በመማማር የራሳቸውን መረዳት ከፍ ለማድረግም ሆነ ላሎች እንዲረዳ ለማገዝ አብረው የሚሰሩበት አውድ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ድግግፋዊ መማር በአዎንታዊ አቻዊ ግንኙነትና እርስ በእርስ መደጋገፍ ከፍ ወዳለ የመማማር ውጤታማነት ለመድረስ የሚያግዝ ብልሃት ነው፡፡

### 5. ብጤን ማስተማር

ብጤን ማስተማር አንደ አሳታፊ ማስተማሪያ ብልሃት ሲሆን በዚህ ብልሃት በመታገዝ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ አቻዎቻቸውን በማስተማር ሂደት ራሳቸውም እውቀት እንዲገበዩ የሚደረግበት ፍላጎትን ከፍ ለማድረግ ጠቃሚ ሂደት ነው፡፡ ይህ ስልት ተማሪዎች የግል ተሞክሮዎቻቸውን ከጥልቅ መረዳት ጋር ለማጣመር የሚረዳቸው ነው፡፡ ስልቱ ተማሪዎች ከመምህራቸው ግብረ-መልስ ማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ መደራጀት ይኖርበታል (ICDR, 2009)፡፡

### 6. ማነቃቃት

ማነቃቃት ተማሪዎች ሀሳብ ማመንጨት እንዲችሉ ለማድረግ በሰፊው ታዋቂ አገልግሎት ያለው ብልሃት ነው፡፡ ተማሪዎችን በማነቃቃት በተደገፈ የመማር ክንዋኔ በርካታ የተለያዩ ሀሳቦችን በአጭር ጊዜ ሊያመነጩ ይችላሉ (Fine, 2003፣ Tomlinson, 2007)፡፡ ማነቃቃት ተማሪዎች በአንድ የተወሰነ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳቦቻቸውን በነጻነት እንዲያንጸባርቁ ለማድረግ እንዲሁም መምህሩ ተማሪዎቹ በቀረበው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ከማነቃቃት ብልሃት ትግበራ ጋር ተያይዞ መታወቅ ያለበት በተማሪዎቹ የሚሰጡ አስተያየቶችን ሁሉ መቀበል፣ በአስተያየቶች ላይ ትችት ከማቅረብ መቆጠብ፣ አንደ አስተያየት ሰጪ ተማሪ ሌላው ተማሪ በሰጠው አስተያየት መነሻ የማዳበሪያ ሀሳብ ሊያቀርብ መቻል

እንዲሁም ይህ ክንዋኔ ከ10 ደቂቃ የበለጠ ጊዜ መውሰድ የሌለበት መሆኑን ነው (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005፣ Tomlinson, 2007)፡፡

### 2.4.7. የተለያዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን መገልገል

በሰፋው እንደሚታወቀው መማሪያ ክፍል የቋንቋ ልምምዶችን ለማካሄድና ለመማር ዋንኛው ስፍራ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከልማዳዊው ማስተማሪያ ዘዴ ተለቀው ልዩ ልዩ አውዳዊ ተግባራትና ክንውኖችን ለተማሪዎቹ ማቅረብ፣ አገላሎጾችንና ድርጊቶችን በድርጊት ጭምር እንዲለማመድ ማድረግና ተማሪዎችን ማነቃቃት ይኖርባቸዋል ((Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008፣ Tomlinson, 2005)፡፡ የቋንቋ ትምህርት ዋንኛ ግብ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማሳደግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ተግባቦት የሚገለጸው በቋንቋ መማሪያ አውድ ከሚቀርቡ ተግባራት ጋር በመቀናጀት መሆን ይኖርበታል፡፡ መስህባዊ የሆኑ የቋንቋ ተግባራት ተማሪዎቹ በማስመሰል፣ ሚና በመጫወት፣ ተግባቦት በማካሄድ፣ ወዘተ ተማሪዎቹን ለማሳተፍ ይረዳል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃትና ተፎካካሪነት ለማሳደግ አይነተኛ አስተዋጽኦ አለው (Wright, 2016፣ Huang, 2011)፡፡ ይህም ቀደም ሲል በ ICDR (2009) እና MOE (2004) የቀረቡትን ሃሳቦች የሚያጠናክር ነው፡፡

### 2.4.8. ለተማሪዎች እውቅና መስጠትና መሸለም የሚሉ ናቸው፡፡

Lincoln የተባለ አዋቂ እንደገለጸው ‹‹እያንዳንዱ ሰው ሽልማት መፈለጉ የሰው ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነው፤ በጣም የሚሳበው ግን ለአድናቆት ነው፡፡›› ተገቢ የሆነ እውቅና በራሱ እንደሽልማት የሚቆጠር ነው፡፡ በተለይ ለተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ከፍ ያደርግላቸዋል፤ የመማር ፍላጎታቸውን ለማነሳሳትም መጠነ ሰፊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ቀጣይ የሆነ የማበረታቻ ስልት መኖር ተማሪዎች በደስተኛነት መንፈስ ለውጤታማነት በይበልጥ እንዲሰሩ ፍላጎት ይፈጥርባቸዋል (Wright, 2016፣ Huang, 2011)፡፡

## 2.5. ማበረታቻን ለቋንቋ መማር ፍላጎት ግብአት የማድረግ ጠቀሜታ

ጥናቶች እንደጠቆሙት፣ ማበረታቻ ለተማሪዎች የመማር ፍላጎት መጎልበት እጅግ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው መሳሪያ ነው፡፡ የማበረታቻ ስልቶች ለተማሪዎች ንቁ መማር ግብአት በሚደረጉበት አውድ የተማሪዎችን ኢ-ንቁነት ባህሪን በማስወገድ አለያም በመቀነስ ለሚማሩት ትምህርት የተሻለ አስተውሎት ወይም ትኩረት እንዲሰጡ ያግዛል፡፡

በማበረታቻ ስልቶች በሚገባ የታገዙ ተማሪዎች በሰፊው ይነቃቃሉ፤ ይበረታታሉ፤ ለመማርም ጉልህ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ የተማሩትን የማስታወስ ችሎታቸው መሻሻል ስለሚያሳይ ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005፣ Tomlinson, 2007)፡፡
ተማሪዎች በሰፊ ጥረታቸው ታግዘው፣ በልዩ ልዩ ተግባራትና ልምምዶች ታግዘው ተምረው የሚያገኙት ከፍተኛ ውጤት ይበልጥ ደስተኛ እንዲሆኑና እንዲበረታቱ ያደርጋቸዋል (Tomlinson, 2005)፡፡ ይህም ቀጣይ ለሆነ የረጅም ጊዜ የመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ገንቢ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የረጅም ጊዜ የመማር ፍላጎትና ተበረታችነት በአካዳሚኩ መስክ ቀጣይነት ያለው አእምሯዊ እድገትና መሻሻል ለማሳየት እንዲሁም እውቀትናና ክህሎትን ለመገብየት ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ (Bainbridge, 2014፣ Tomlinson, 2005)፡፡
እውቀትና ክህሎትን የመገብየት ሂደት ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው ማወቅንና መበረታታትን ይጠይቃል (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡ ስለዚህ በመማር ጥረታቸው የተበረታቱ ተማሪዎች ስለ መማር ሂደት ሰፊ ግንዛቤና ተግባራዊ ተሞክሮ ይኖራቸዋል፤ በአካዳሚክ ተግባሮቻቸው ከሌሎች መሰሎቻቸው በጣም በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተለያዩ ክንዋኔዎችን በብቃት የመወጣት ባህሪም ያዳብራል (Kolb & Kolb, 2009፣ McClanaghan, 2008)፡፡

## 2.6. ፍላጎት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ

ታላሚውን ቋንቋ የመማር ፍላጎትና ምኞት ያደረበት ተማሪ ጥረት ካሳየ በቋንቋ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግብ ይታመናል፣ በቋንቋው የመጠቀም ጥሩ ችሎታም ሊኖረው ይችላል፡፡ በፍላጎት ዙሪያ ከተከናወኑት የምርምር ስራዎች መካከል እያንዳንዱ የፍላጎት ዓይነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ በሚመለከት ረገድ የመጀመሪያው ምርምር በጋርድነርና ላምቤርት (1972) በፊሊፒንስ የተካሄደ ጥናት ነው Brown, (2000). Ellis (1994)፡፡ ፍላጎት ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶም ይገልጻሉ፡፡

## 2.7. የፍላጎት ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች

የ Hidi እና Renninger ባለ አራት ገጽታ የፍላጎት እድገት ሞዴል የተሟላ እና በሰፊው እውቅና ያገኘ የቀለም ትምህርትን ፍላጎት መሰረተ-ሃሳብ የሚያሳይ ንድፈ-ሃሳባዊ ሞዴል ነው፡፡ የፍላጎት ጥናት ፈር ቀዳጅ የሆነው Herbart (1776—1841) ፍላጎትን ከቀለም ትምህርት ጋር በማያያዝ ለትምህርት አላማ ግባዊነት ካለው ጠቀሜታ አንጻር ካመላከተ በኋላ፣ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች ፍላጎት ለተማሪዎች ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ ሲፈትሹ ቆይተዋል፡፡

በዚሁ መሰረት በበርካታ አጥኚዎች ፍላጎት የተማሪዎችን ብቃት፣ ቅልጥፍና፣ ጥረት ከፍ ለማድረግ፣ የትምህርት ተሳትፎን ለማጠናከር፣ የመማር ቀጣይ ተነሳሽነትን ለመጠበቅ ያለው ጠቀሜታ እውቅና ተሰጥቶታል (ምሳሌ፡- Guo & Zhang, 2012፣ Walkington & Sherman, 2013፣ Tomlinson, 2007)፡፡

በምዕራባውያን ዘንድ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ደረጃና የውጤት ተዛምዶ ለመለካት የሚያገለግል በርከት ያለ ግለ-መሳሪያዎች (self-report instruments) ተዘጋጅተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡ ከእነዚህ አብዛኛዎቹ መለኪያዎች /ስኬሎች/ ውስን በሆነ መልኩ ስሜታዊነትን (emotion) ወይም የዋጋማነት ምንዝሮች (value components) በመማር ፍላጎት ያለውን ተጽእኖ ለመፈተሽ የረዱ ናቸው፡፡ (Hidi & Harackiewicz, 2008)፡፡
የመማር ፍላጎት ልዩ የሆነ መነቃቃት ላይ የሚመሰረት ተለውጦ ሲሆን ተማሪዎች የሚወዱት ወይም የሚመርጡት የመማሪያ ይዘትና ግብአትን ከተወሰነ የትምህርት ግብ፣ ተግባርና ልምምድ ጋር አሰናኝቶ ለተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ዝግጅት በሚመጥን ቅንጅት ማቅረብን የሚጠይቅ አሰራር ነው፡፡ (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በሰው--ቁስ (personobject) ንድፈ-ሃሳብ መሰረት የፍላጎት እድገት ጽኑ መሰረት በወቅቱ የሚካሄደው የሰውና ቁስ የአውድ መስተጋብር ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ፍላጎት ሁኔታዊ (situational) እና ግለሰባዊ (individual) ፍላጎት ተብል በሁላት ፈርጆች ይከፈላል፡፡ (Justina, 2015፣ Hidi, 2010)፡፡
ሁኔታዊ ፍላጎት አውድ ተኮር በሆነ መልኩ ለቀረበው ጉዳይ ትኩረት መስጠትንና ስሜታዊ በሆነ መንገድ መስተጋብር ለማካሄድ የተያዘ ፍላጎትን ያመለክታል፡፡ (Hidi, 2010፣ Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በሌላ በኩል ግለሰባዊ ፍላጎት ደግሞ ለአንድ የተወሰነ ይዘት ቀጣይነት ያለው ፍላጎት ይዞ መገኘትን የሚወክል ብያኔ ነው፡፡
ግለሰባዊ ፍላጎት ከአውዳዊ ፍላጎት በመነሳት /በመመንጨት/ በየጊዜው የሚያድግ ባህሪ ነው፡፡ (Hidi and Renninger, 2006)፡፡ በዚሁ መሰረት ምንም እንኳን ግለሰባዊ ፍላጎት ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ባህሪ ቢሆንም፣ ሁለቱም የፍላጎት አይነቶች አዎንታዊ በሆነ መልኩ የተማሪዎችን የመማር ትኩረት ለመሳብ፣ አእምሮአዊ ክንውኖችን ለማሳለጥ እና የሚያከናውኑትን ተግባር እንዲወዱት በማድረግ ረገድ ገንቢ ተጽእኖ ያላቸው ናቸው፡፡ (Hidi, 2010፣ 2013)፡፡
በዚህ መሰረት ብልጹግ ግለሰባዊ የመማር ፍላጎት በቀጣይ አራት ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነዚህም፡- ከፍተኛ ስሜት፣ እሴታማነት፣ እውቀትና ተሳትፍ ማድረግ ናቸው፡፡
የከፍተኛ ስሜት ምንዝሮች የሚያመለክቱት በተግባራት ዙሪያ አዎንታዊ ስሜት መኖርን ነው፡፡

ለምሳሌ፦ተደሳችነት፣ መቀስቀስ፣ ፍክ ስሜት ውስጥ መገኘት ይጠቀሳሉ (Hidi and Renninger, 2006)፡፡

የእሴታማነት ምንዝሮች የሚያመለክቱት የሚያከናውኑት ተግባር ምን አይነት ጠቀሜታ እንደሚያስገኝላቸው መገንዘብን ነው፡፡

(ለምሳሌ፡- በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጻፍን መለማመድ ለአለማቀፋዊ ተግባቦት ያለውን አስተዋጽኦ ማወቅ)፣ Hidi and Renninger, 2006)፡፡

የእውቀት ምንዝሮች የሚያመለክቱት በተወሰነ የትምህርት መስክ የእውቀት ክምችት ባለቤት ሆኖ የመገኘት ፍላጎትን ነው፡፡ Tomlinson (2007) እንደጠቆሙት፣ የእውቀት ክምችት ባለቤትነት ከፍላጎት ጋር አዎንታዊ ቀጥተኛ ተዛምዶ ያለው ነው፡፡ የተሳትፍ ምንዝሮች የሚያመለክቱት በአንድ የተወሰነ የመማር ክንዋኔ ውስጥ ንቁ የተሳታፊነት ዝንባሌን አስቀድሞ ለመተንበይ የሚረዳ ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነ ግለሰባዊ ፍላጎት ያዳበሩ ተማሪዎች በበርካታ የመማር ተግባራት የመሳተፍ ተነሳሽነት ይዘው የሚገኙ ናቸው፡፡ እንደ Omrod (2008) ገለጻ፣ ተሳትፎ ፍላጎትን በማስቀጠል፣ በማጠናከርና በማጥለቅ አንድን የተወሰነ የመማር መስክ በስፋት ለማወቅ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡

## 2.7. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በቋንቋ ትምህርት ሂደት አራቱ መሠረታዊ የቋንቋ ክሂሎች (የማንባብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር እና የማዳመጥ) ክሂሎች ቁልፍ የሆኑና ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡ በተለይ የምንበብ ፍላጎት በማንኛውም የትምህርት መስክ አስፈላጊ መሆኑ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች አላስፈላጊ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ማነበብ ክሂል መማር ፍላጎት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የተለያዩ ምሁራን ያጠኑትን ጥናት ስንመለከት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለው ዝቅተኛ ውጤት ከፍተኛ ደረጃ ላ ለው ደግሞ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግብ እንደሆነ ከፍ ሲል በጽንሰ ሀሳባዊ ዳሰሳ ክፍል ተቃኝቷል፡፡

ለተማሪዎቹ የማንበብ ክሂል ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን አንዳንዶቹ በጥናታቸው እንዳመለከቱት መንስኤው የማንበብ ክሂል ፍላጎት ማነስ፣ ሌሎቹ ደግሞ የትምህርት አሰጣጥ ችግር መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድ በተደረገው አሰሳ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውን የእታገ (2013) ጥናትንና ሌሎች በማንበብ ክሂል መማር ፍልጎትና ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ይዘት የተሠሩ ተቀራራቢነት ያላቸውን ሌሎች የጥናት ሥራዎች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

እታገ (2013) የንባብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ በኦሮምኛ ቋንቋ አፌቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዱምቱ ሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚልሠርታለች። በጥናቱ የተማሪዎች የንባብ ፍላጎትና የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ውጤት ተዛምዶ የጠበቀ እንደሆነ ተገልጿል።

ይህ ጥናት ከእታገ ጥናት ጋር የንባብ ፍላጎትና የማንበብ ክሂል ውጤት ተዛምዶ መፈተሹና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው አንድ መሆኑ የሚያመሳስለው ይሆናል። ይህን የጥናት ሥራ ከእታገ ሥራ ልዩ ከሚያደርጉ ነጥቦች ጥቂቶቹ ቀጥለው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

የእታገ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በዱምቱ ሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ላይ ሲሆን ይህኛው ጥናት ግን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በዳውሮ ዞን፣ ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ መሆኑ ነው። የአታገ ጥናት ለጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ የጥናት መላምቶች መነደፋቸው ሌላው ልዩነት ነው። የብርሃን ጥናት ይዞት የተነሳውን ዓላማ ለማሳካት የተጠቀመው የጥናት ስልት ገላጭ የምርምር ስልትና በከፊል ፍትነታዊ የምርምር ዘዴ የተጠቀመች ሲሆን ይህ ጥናት ዓላማውን ለማሳካት ተዛምዷዊ (Correlational) የምርምር ስልት የተጠቀመ መሆኑ ልዩ የሚያደርጉ ነጥቦች ናቸው። በሌላም በተገኘው ውጤት አንጻር የእታገ ጥናት የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት (74.16) ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ደግሞ (49.76) ሲሆን የ24.4 አማካይ ውጤት ብልጫ ያስመዘሀበ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በ (SPSS Software Version 26) በተደረገው ትንተና የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት (73.6%) በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ (70.23%) በ 3.37% ልዩነነት ያሳየ መሆኑ ልዩ ያደርጋል።

በሌላ መልኩ የእታገ መረጃ ትንተና እንደሚያሳየው የተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ውጤት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚፈረጅ ሲሆን በዚህ ጥናት መረጃ ትንተናው ክፍል ላይ

እንደተመለከተው የተተኳሪ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፍተና ውጤት መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በረከት (2010) በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢ-አፍፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የተሠራ ጥናት ሲሆን የትናቱ ይዘት በንባብ ክሂልና ተዛምዶ በመሆኑ እንዲሁም የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ ስለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

የበረከትን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ የሚያደርጉት ነጥቦች፡- ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ፣ ጥናቱ ትኩረት ያደረጋቸው ክፍል ተማሪዎች፣ እንዲሁም ይዞት የተነሳው ዓላማ፣ የበረከት ጥናት ዓላማውን ለማሳካት ገላጭ ስልትን የተጠቀመ ሲሆን ይህ የጥነናት ሥራ ደግሞ ተዛምዷዊ (Correlational) ስልት የተጠቀመ መሆኑ፣ የበረከት ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ፈተናንና ቃለ መጠይቅን የተጠቀመ ሲሆን በዚህ የጥናት ሥራ በመረጃ መሰብሰቢያነት አንብቦ የመረዳት ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ ተግባራዊ ማድረጉ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ክፍሌ (2002 ዓ.ም) እና አለምነሽ (2001 ዓ.ም) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምድ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል፡፡ ጥናቱ ጥቅል ብሆንም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ማዕከላዊ ጉዳይ ማድረጉ፣ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍ መጠቀሙ፣ የጽሑፍ መጠይቅንና ፈተናን ለመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀሙ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይዞት ከተነሳው ዓላማ፣ ጥናቱ ከተካሄደበት ቦታና ጊዜ፣ ከጥናቱ ተሳታፊዎች፣ ከአነሳሽ ምክንያት ከዚህ ጥናት የሚለያይ ነው፡፡ በዋናነት ክፍሌ እና አለምነሽ ጥናት ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲለይ ያደረገው ጉዳይ፡- በክፍሌ እና አለምነሽ ጥናት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማር ውጤት በምሁራኑ ደረጃ ምደባ መሠረት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ጥናት የተማሪዎች የንባብ ከረሂል ወጤት መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ትንተናው ያሳያል፡፡ ሌላው ልዩነት በክፍሌ በትንተናው አማርኛ የመማር ፍላጎት ውጤት፣ አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ የመረዳት ክሂል

በማለት በአራት ከፋፍሎ ለትንተና ያቀረበ ሲሆን በዚህ ጥናት የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተብሎ በጥቅሉ ለትንተና ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለመቃኘት እንደተሞከረው በፍላጎት፣ በሁለተኛ ቋንቋ መማርና በትምህርቱ ውጤታማ መሆን/አለመሆን ላይ በየጊዜው በተለያዩ ተመራማሪዎች፣ በተለያዩ አካባቢዎች፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡ ሁሉንም በጋራ የሚያስማሙ ግኝቶች አለ ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ከዚህ የጥናት ሥራ ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት ያለው የእታጉ ጥናት ሥራ ሲሆን ሌሎች ሥራዎች የአማርኛ ትምህርት መማር ፍላጎት የማንበብ ኪሂል ስለ መማር ፍላጎት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ የጥናታቸው ተለዋዋጭ (Variable) ስላደረጉ ለዚህ ጥናት በተዛማጅነት ቀርበዋል፡፡ ከዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ስኬትን በተመለከተ አሁንም በፍላጎትና በውጤት መካከል ተዛምዶ ላይ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ጥናቱን ለማካሄድ በቀዳሚነት አነሳስቷል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ እና ንድፍ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዳውሮኛ ቋንቋ አፌቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት መመርመር ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት እንዲያስችለው በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ አካቶ ይዟል፡፡ የጥናቱ ዘዴ በስሩ ያካተታቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የመረጃ ምንጭ፣ የናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል እና የመረጃ አተናተን ናቸው፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በአይነቱ መጠናዊ ምርምር (Quantitative Research) ሲሆን፣ ጥናቱ ተዘምዷዊ (Correlational) የምርምር ስልትን የተከተለም ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ማንብብ ክሂል መማር ላይ ያላቸው ፍላጎት እና ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛልዶ ምን እንደሚመስል በተመለከተ የተዛምዶ መጠን በመጠቆም ተመራጭ የምርምር ስልት በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲባል ሌሎች የምርምር አይነቶች ለችግሮች የመፍትሔ ሀሳብ አያቀርቡም በማለት ሳይሆን ተዛምዷዊ የምርምር ዘዴ፤ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሌሎች የምርምር ዘዴዎች በተሻለ የሚጠቅም እንደሆነ ስለታመነበት ነው፡፡ በተጨማሪም መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ማንበብ ክህል መማር ፍላጎት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ ለማጥናት ስለሚጠቅም ነው፡፡

### 3.2. የጥናቱ አካላይ

"የጥናቱ አካላይ ሲባል ጥናቱ የሚካሄድበት፣ የተማራማሪው ትኩረት ያረፈበትና ችግሩ የተከሰተበት አጠቃላይ የተጠኝዎችን ቁጥር ያቀፈ ነው" ያለው (2009፤ 119)፡፡

ስለሆነም የዚህ ጥናት አካላይ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙት ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የተመረጠው ደልቫ ሁለተኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነው ጭጮ ሁለተኛና መሠናዶ ትምህርት ቤት

ያልተመረጠበት ምክንያት ከአጥኚው የሥራ ቦታ ርቀት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ የቦታ ርቀትም አጥኚው መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት የመረጃ ክፍተት ከማምጣቱም በተጨማሪ ከአጢኚው ከገንዘብ አቅም በላይ ስለሚሆንም ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረትም የዘጠነኛ ክፍል በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክህል ፍላጎት ከውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶን መፈተሽ ነው፡፡

### 3.3. የጥናቱ የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሆነዉ ያገለገው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ ዞን በገሳ ከተማ አስ/ር ደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡

### 3.4. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

"ናሙና ስንል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባላት በሙሉ በመውሰድ በጥናታችን ተሳታፊ ለማድረግ ሳንችል ስንቀር ወይም ማሳተፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ነገር ግን አጠቃላዩን ብንወስድ ልናገኝ እንችላለን ብለን የሚናስበውን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰዎችን (ነገሮችን) ሥርዓታዊና ተጠየቃዊ መንገዶችን በመከተል መርጠን በጥናታችን እንዲካተቱና መረጃ እንዲሰጡን የሚናደርጋቸው ጥናቱ አካላይ ውስን ክፍል ናቸው፡፡ በቁጥር ከአካላዩ አብዘኛውን ጊዜ ያንሳሉ" ያለው (2009፤ 120)፡፡ እንደ ያለው ገለጻ በናሙና አመራረጥ ወቅት ተመራማሪዎች ሁለት ዓይነት ዓብይት የንሞና ዜዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህም እድል ሰጭ ንሞና (Random or probability sampling) እና ወሳኝ ንሞና (Non probability sampling) ናቸው፡፡

ከነዚህም ይህ ጥናት እድል ሰጭ ንሞና (Random or probability sampling) ዘዴን በመጠቀም አጥኝው ጥናቱን አካህዷል፡፡

#### 3.4.1. የከተማ አስተዳደሩ ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ ዞን ሲሆን በዳውሮ ዞን 10 ወረዳዎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደር ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የገሳ ከተማ አስተዳደርን በአመቺ ንሞና ዘዴ (Convinance Sampling) በመጠቀም ተመርጧል፡፡ ይህ ከተማ አስተዳደር የተመረጠበት ምክንያት የአጠኚው የመኖሪያ አካባቢ እንዲሁም የሚሰራበት አከባቢ ስለሆነ ምርምሩን ለማካሄድ ሊገጥመው ከሚችል የአካባቢ እንግድነት፣ የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንጻር

በአጥኚው መገኛ ከተማ አስተዳደር ጥናቱን ማካሄድ አመቺ በመሆኑ እንዲሁም ለስራው ተባባሪና ፈቃደኛ መምህራንና ተማሪዎች በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ለማግኘትና የጥናቱን መረጃዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሰብሰብ ያስችላል የሚል እምነት ስላለው ነው፡፡

### 3.4.2. የትምህርት ቤቱ ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተከናወነው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ ዞን በገሳ ከተማ አስ/ር ሲሆን በከተማ አስ/ሩ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይገኛሉ፤ ከነዚህ ት/ቤቶች የደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለጥናቱ ተመርጧል፤ትምህርት ቤቱም የተመረጠው በአመቺ የናሙና አወሳሰድ (Convenience Sampling) ስልት ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ ስልትን የተከተለ በመሆኑ የትኛውም ትምህርት ቤት ቢመረጥ መስራት ይቻላል፡፡ ሆኖም ለአጥኚው የስራ አካባቢ ቅርብ በመሆኑ ጥናቱን በቅርበት ለመከታተል፣ በጥናቱ የሚሳተፉ መምህራንና የተማሪዎችን መረጃ የመስጠት ትብብር ለማግኘት በማሰብ በገሳ ከተማ የሚገኘው ደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥናቱ እንዲካሄድበት ፈቃደኛ ሆኖ ስለተገኘ ተመርጦ ወደ ጥናቱ ተገብቷል፡፡

### 3.4.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በአመቺ የናሙና አወሳሰድ (Convenience Sampling) ስልት ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በመማር ላይ ያሉ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆን፣ በዚህ ዓመት በት/ቤቱ ዘጠነኛ ክፍል ስድስት መማሪያ ክፍሎች ማለትም (A-F) የሚገኝ ሲሆን በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ከ A-E ድረስ በእያንዳንዱ 33 (ሰላሳ ሶስት) ተማሪዎች በዘጠነኛ F ክፍል ደግሞ 35 (ሰላሳ አምስት) በአጠቃላይ በስደስቱ መማርያ ክፍሎች 200 ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች ከእያንዳንዱ ክፍል በቀላል ዕጣ ናሙና 10 ተማሪዎችን ከስድስት ክፍል ደግሞ 60 (ስልሳ) ተማሪዎችን ለጥናቱ መረጃ ሰጭነት እጥኚው መርጠዋል፡፡ የክፍል ደረጃውም የተመረጠበት ምክንያት በት/ቤቱ አስራ አንደኛ እና አስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባለመኖሩ እና ዘጠነኛ ክፍል ለሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያው ክፍል በመሆኑ በዘጠነኛ ክፍል ላይ ቢሰራ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይቻላል በማለት እና መምህራን ደግሞ የተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህል መማር ፍላጎትን ለይተው በማወቅ ለአስረኛ ክፍል የማንበብ ክህል ትምህርትን ተማሪዎች በሚፈልጉት መልክ ያቀርባሉ ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡ ሌላው ምክንያት በትምህርት ቤቱ ሁለተኛ ቋንቋ የሚሰጠው በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ብቻ ላይ ሲሆን አሥረኛ ክፍል እንዳይመረጥ ሁለት ክፍል ብቻና

የተማሪዎች ቁጥር አንስተኛ በመሆናቸው ሙሉ መረጃ ማግኘት አልችልም በሚል አጥኚው ስላመነበት ነው፡፡

### 3.4.4. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ንሞና አመራረጥ

በዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ስድስት መማሪያ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን፣ ከA-E ድረስ በእያንዳንዱ የዘጠነኛ መማሪያ ክፍል ውስጥ 33 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በF ክፍል ደግሞ 35 በድምሩ 200 ተማሪዎች በ2016 ዓ/ም እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ይህም በመሆኑ በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ከስድስቱ ክፍሎች ከእያንዳንዱ ክፍል 10 ተማሪዎችን በድምሩ 60 ተማሪዎችን ከተለያዩ ክፍልች አውጣጥቶ መረጃ ለመውሰድ አጥኝው መርጠዋል፡፡ ምክንቱን ከሁሉም ተማሪ መረጃ ለመውሰድ አስቸጋሪና ጥናቱም ተንዛዛ ስለምሆን እና የተማሪ ቁጥር 30% በመውሰድ ጥናቱን ብሠራ ጥናቱ ሙሉ መረጃ ምግኘት ይቻላል ብለው አጥኚው ስላመነበት ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 1፡ የተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

| የትምህርት ቤቱ ሥም | የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ ተማሪዎች ብዛት | | | | | | በቀላል የዕጣ ናሙና የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | % | ሴ | % | ድ | % | ወ | % | ሴ | % | ድ | % |
| ዳልቫ 2ኛ ደረጃ | 9ኛ | 120 | 60 | 80 | 40 | 200 | 100 | 36 | 60 | 24 | 40 | 60 | 100 |

### 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት ስኬት የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶን ለመፈተሽ የተፈለገ ስለሆነ ማንበብ ክሂል ውጤትን ለመለካት ለተማሪዎች ምንባብ ተዘጋጅቶ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ተፈትነዋል፡፡

የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎትን ለመፈተሽ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች በማዘጋጀት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጁ መጠይቆች የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የሚመለከቱና ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር የሚዳስሱ መጠይቆች ናቸው፡፡

የተዘጋጁ የምንባብ ጥያቄዎች የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ውጤት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃ ለማግኘት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## 3.6. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በጥናቱ ዓላማ መሠረት የተመረጡት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የፍላጎትን መጠን መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ እና የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና የንባብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶን ለመፈተሽ የተፈለገ ስለሆነ የማንበብ ክሂልን ለመለካት ለተማሪዎች ምንባብ ተዘጋጅቶ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ተፈትነዋል፡፡

የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት ለመፈተሽ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች በማዘጋጀት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጁ መጠይቆች የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት የሚመለከቱና ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር የሚዳስሱ መጠይቆች ናቸው፡፡

ለዚህም ስባል የጽሑፍ መጠይቁን እንድሞሉና እና የማንበብ ክሂል ፈተናን እንዲፈተኑ የተመረጡት ዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ከስድስት መማሪያ ክፍሎች 60 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ቀጥሎ በተማሪዎቹ መካከል ሊኖር የሚችለው የተለያየ የመረዳት ባህሪ ተላውጦ በጥናቱ ውጤት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተዛምዶን ለመፈተሽ ሲባል አንጻራዊ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፉ ማድረግ በማስፈለጉ ከ9ኛ A እስከ E ክፍሎች ከእያንዳንዱ 33 /ሰላሳ ሶስት/ ተማሪዎች እና ከ9ኛ F ክፍል ደግሞ 35 /ሰላሳ አምስት/ ተማሪዎች በድምር 200 /ሁለት መቶ/ ተማሪዎች መካከል ከእያንዳንዱ ክፍል 10 /አስር/ ተማሪዎች በድምሩ 60 /ስልሳ/ ተማሪዎችን በቀላል ዕጣ ናሙና  የማጣራትና ወደ ጥናቱ አውድ የማምጣት ስራ ተከናውነዋል፡፡

### 3.6.1. የማንበብ ክሂል ፈተና

በአንድ የክፍል ደረጃ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ውጤትን ለመለካት ከሚያገለግሉ የመረጃ መሳሪያዎች አንዱ የምንባብ ክሂል ፈተና ነው፡፡ ይኸዉም ምንባቡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ጊዜ ከተነባቢነቱ በተጨማሪ ስነ ልሳናዊ የክብደት ደረጃዉ፣ ባህላዊ አውድ፣ አሳታፊነቱ እና ተማሪዎቹ ለንባብ ያላቸዉ ፍላጎት ከግንዛቤ መግባት እንዳለበት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የምንባብ ፈተናዎች የማንበብ ፍላጎትን ለመለካት የጽሑፍ መጠይቅ ከሞሉት በኋላ ተሰቷል፡፡ የምነበብ ክሂል ፈተናው  እርማቱ የሚከናወነው ከ30 ነጥብ /ማርክ/ በመስጠት ይሆናል፡፡ በቀረበው ምንባብ እና ከምንባቡ የተውጣጡ በአጠቃላይ 30 ጥያቄዎች የምንባብ ፈተና መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የፈተናዎችን አዘገጃጀት በተመለከተ ከምንባቡ ላይ የተመሰረተ ከምንባቡ 30 /ሰላሳ/ ጥያቄዎች ተውጣጥተው የቀረቡ ሲሆን፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚለኩ ጥያቄዎችን እንዲያካትቱ ተደርጓል፡፡ የጥያቄዎቹ ብዛት በአጠቃላይ 30 ሲሆን፣ 12 እውነት/ሀሰት፣ 12 ምርጫ ሰጪ፣ 6 ክፍት ቦታ መሙላት የሚሉ ናቸዉ፡፡

የተዘጋጁ የምንባብ ክሂል ጥያቄዎች የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃ ለመስጠት እና ከማንበብ ፍላጎት ጋር ያለው ተዛምደው ምን ያክል እንደሆነ ለመፈተሽ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ፈተናው በአጥኚው የተዘጋጀ ሲሆን ትክክለኛነቱን ልምድ ባላቸው በትምህርት ቤቱ መምህርት እና በአማካሪ ታይተው ማስተካከያ ተሰትተውበታል፡፡ ፈተና ለተማሪዎች ከጽሑፍ መጠይቅ በኋላ ተሰጥተው በአጥኚውና በመደበኛ መምህርት እርማት ተደርጓል፡፡

### 3.6.2. የጽሐፍ መጠይቅ

ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የማንበብ ክሂል ፍላጎት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ፍላጎት መለኪያ ስር የሚመደቡ፣ በትምህርቱ የተካተቱት ዝርዝር ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ 20 ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ ከሁሉም ሰክሽን ለተመረጡ ተማሪዎች ብቻ ተሞልቷል የጽሑፍ መጠየቁን የሞሉት 60 ተማሪዎች ናቸው)፡፡

የማንበብ ፍላጎት አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁ ዋና ዓላማው ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትን ከመማራቸው በፊትና ከትምህርቱ በኋላ የማንበብ ፍላጎት መጠናቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና ማንበብ ክሂል ፈተና የሚገኘው ውጤት በርግጥም ምንባቡ የተማሪዎቹን

የፍላጎት መጠን በማሻሻሉ የተገኘ መሆኑን ወይም የምንባቡን ውጤታማነት ለማወቅ ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶን ለመተሸ ነው፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ሶስት አይነት ይዘት ያለው ማለትም 8 (ስምንት) አጠቃላይ ፍላጎትን የሚመለከት፣ 6 (ስድስደት) የማንበብ ፍላጎት የሚመለከት እና 6 (ስድስት) የንባብ ችሎታ አሳሽ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ በዚህ የምርምር ስራ የጥናቱ ተሳታፉዎችን የማንበብ ፍላጎት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶን ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

የመጠይቅ ጥያቄዎቹ ሙሉ በሙሉ የሊከርት ስኬል የጽሁፍ መጠይቅ አቀራረብ ስልትን በመከተል ከ‹‹በጣም አልስማማም›› እስከ ‹‹በጣም እስማማለሁ›› ባለአምስት አማራጭ መልሶችን ይዘው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ‹‹በጣም እስማማለሁ›› (5 ነጥብ)፣ ‹‹እስማማለሁ›› (4 ነጥብ)፣ ‹‹መወሰን ያስቸግረኛል›› (3 ነጥብ)፣ ‹‹አልስማማም›› (2 ነጥብ)፣ እና ‹‹በጣም አልስማማም›› (1 ነጥብ) ይዘዋል፡፡ ይህም ተሳታፊዎቹ በተቀላጠፈ አኳኋን መጠይቁን ሞልተው እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ረድቷል፡፡

#### 3.6.2.1. የጽሑፍ መጠይቅ ተገቢነትና አስተማማኝነት

የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ከዚህ ቀደም በትምህርት ቤትና በዩኒቨርሲቲ በስራ ላይ ውሎ ተግባራዊነቱ የተረጋገጠ ከNational Research Council (2003) እና Schiefele (2008) አጠቃላይ የመማር ፍላጎት እና አንብቦ የመረዳት መጠይቆችን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመመለስ ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ አድርጎ አጣጥሞ የመጠቀም አቅጣጫን ጥናቱ ተከትሏል፡፡

በዚሁ መሰረት ከፍ ሲል የተጠቀሱት ምንጮች ባቀረቧቸው የመጠይቅ ጥያቄዎች በመደገፍ ‹‹አጠቃላይ ፍላጎት››ን የሚወክል 8 /ስምንት/ ጥያቄዎች፣ ‹‹የማንበብ ፍላጎት››ን የሚወክል 6 /ስድስት/ ጥያቄዎች፣ እንዲሁም ‹‹የማንበብ ችሎታ››ን የሚመለከቱ 6 /ስድስት/ ጥያቄዎች በጽሁፍ መጠይቁ ተካተው ቀርበዋል፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ የተካተቱ ጥያቄዎች አጠቃላይ ብዛት 20 /ሃያ/ ነው፡፡ ስለመጠይቁ አሞላል የተጠኚዎቹን ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪነት ግምት ውስጥ በማስገባት አጥኚው አጠገባቸው በመሆን በሁለተኛ ቋንቋቸው ጭምር ማብራሪያ ሰጥተው አስሞልተዋቸዋል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነትና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የመጠይቁን ትክክለኛነት በተመለከተ በማስተማር ረጅም አመት ልምድ ላላል ለ1 አማርኛ ቋንቋ መምህርትን እና የጥናቱ አማካሪዎችን በማሳየት እርማት ተደርጎበት ከተስተካከለ በኋላ ለጥናቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ከመምህርቷ እና አማካሪዎች የተገኘውን

መረጃ መሰረት በማድረግም መጨመር ያለባቸው ተጨምረዋል፣ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለዋል፣ መወገድ ያለባቸው ተወግደዋል፣የአሻሚነት ባህሪ የታየባቸውን በማብራራት ግልጽ የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል፣ የዘርፉ ባለሙያዎችን ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል።

### 3.6.2..2. . የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት

ለአንድ የምርምር ስራ አገልግሎት እንዲውል የተነደፈ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ (መለኪያ) ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ በተቃና፣ በተሟላ እና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዲያስችል የሚያመለክት ከሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውን ትክክለኛነት ያሳያል (ያለው 2006) ።

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አጥኚው የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅመዋል።

የጥናቱ አቅራቢ በጥናቱ ሂደት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት አንደኛው መንገድ ልምድ ባላቸው የዳልሻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ አንድ መምህርትን ደጋግሞ ማሳየት ነው። በጥናቱ ሂደት የጥናቱ አቅራቢ ከአማካሪው ጋር በተደጋጋሚ ጊዜ በመወያየት እና የተገኘውን ግብአት በመጠቀም የተፈለገው የጥናት ግብ እውን እንዲሆን በሚያስችል መልኩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለማስተካከል ጥረት አድርገዋል።

## 3.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተሳታፊዎች የሚገኙት መረጃዎች ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት በአግባቡ የማደራጀትና የማጠናቀር ስራ ተሰርተዋል። በዚሁ መሰረት መረጃዎች ለትንተና በሚያመች መልኩ መለያ ቁጥር ተደርገው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (Code Sheet) ላይ ተሰፍረዋል። የተሰበሰቡትን መጠናዊ መረጃዎች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራ ከተሰራ በኋላ መረጃዎቹ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ባላቸው ግንኙነት መሰረት ተደራጅተው በSPSS Version 26 የመረጃ ማብላያ ቋት በማስገባት ውጤቱ ተተንትነዋል። በዚሁ መሰረት የተሰበሰቡት ንባብ ክህል ላይ ያተኮሩ የፈተና መረጃዎች ትንተና ተካሂዷል። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ወደ ማንበብ ክሂል ፈተና ከመግባታቸው በፊት ያላቸውን የንባብ ክሂል መማር ፍላጎትን የሚጠይቅ መጠይቆችን እንዲሁም ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶን ለመፈተሽ ደግሞ የንባብ ክሂል ፈተና ተፈትነው ውጤቱም በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ አማካይ

ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቶ ቀርበዋል፡፡ የተማሪዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትኖ ከማብራሪያ ጋር ቀርቧል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመተንተንም ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ቀመር ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዚህ ስታቲስቲካዊ ማሳያ በመታገዝ የጥናቱን የመጀመሪያውን መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ለተማሪዎች በቀረበላቸው መጠይቅ የተገኘው ባለ 5 /አምስት ነጥብ/ የሊከርት ስኬል ምላሽ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት እንዲሁም በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህም የጥናቱን የመጀመሪያውን መላምት ለመመለስ ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ

## 4.1. የጥናቱ መረጃ ትንተና

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ አንደኛው የመረጃ መሰብሰቢያ የንባብ ክሂል ፈተና ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ለተጠኚዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት ፈተናው ከ6 /ስድስት/ የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች ከእያንዳንዱ ክፍል 10 /አስር/ አማርኛን ሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች ቀርቦላቸው እንዲፈተኑ እና የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት የተመለከቱ 20 (ሃያ) የጽሑፍ መጠይቆች ለተተኳሪ ተማሪዎች ቀርበው እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡

### 4.1.1. የጽሑፍ መጠይቅ ትንተና

ይህ ክፍል ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ ያገኙትን መረጃ መሠረት በማድረግ ትንተና የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቅ በሶስት ክፍሎች የተዘጋጀ ሲሆን ክፍል አንድ የተማሪዎችን አጠቃላይ የማንበብ ትምህርት ፍላጎት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይለካሉ ተብለው የታሰቡ ሀሳቦች በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ ለመወሰን እቸገራለሁ፣ አልስማማም፣ በጣም አልስማማም በሚሉ አማራጮች የሚመለሱ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ክፍል ሁለት ደግሞ የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትን የሙመለከቱ ሲሆን ክፍል ሦስት ደግሞ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ የሚፈትሹ ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል በዚህ ጥናት ክፍል የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት የተመለከቱ 20 (ሃያ) የጽሑፍ መጠይቆች ለተተኳሪ ተማሪዎች ቀርበው እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በሶስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን አጠቃላይ ፍላጎትን የሚፈትሹ ስምንት መጠይቆች፣ የንባብ ፍላጎትን የሚፈትሽ ስድስት መጠይቆች እና የማንበብ ችሎታ የሚለኩ ስድስት መጠይቆች ናቸው፡፡

## ሰንጠረዥ ሁለት፡- የአጠቃላይ ማንበብን መማር ፍላጎትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ፤

| ተ/ቁ | መጠይቆች | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ ማንበብን መማር ለእኔ አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡ | 60 | 22 | 36.7 | 16 | 26.7 | 10 | 16.6 | 8 | 13.3 | 4 | 6.7 |
| 2 | አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተግባቦት እና የሥራ እድል እንደሚያሰፋልኝ አውቀዋለሁ፡፡ | 60 | 23 | 38.33 | 21 | 35 | 11 | 18.33 | 3 | 5 | 2 | 3.34 |
| 3 | በትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ የማንባብ ችሎታዬን ለማሳደግ ምቹ እድል አለኝ፡፡ | 60 | 20 | 33.33 | 23 | 38.33 | 5 | 8.34 | 7 | 11.66 | 5 | 8.34 |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክህል መማር በጣም ያስደስተኛል፡፡ | 60 | 26 | 43.33 | 22 | 36.66 | 8 | 13.33 | 2 | 3.34 | 2 | 3.34 |
| 5 | ስለ ማንባብ ክህል መማር ለኔ አድስ ነገር እንደማወቅ የሚያስደስት ክዋኔ ነው፡፡ | 60 | 21 | 35 | 19 | 31.66 | 8 | 13.34 | 7 | 11.66 | 5 | 8.34 |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህልን መማር ከተለያዩ መረጃ ምንጮች አንብበ ለመረዳት ምቹ እድል ይፈጥርልኛል፡፡ | 60 | 24 | 40 | 18 | 30 | 5 | 8.34 | 7 | 11.66 | 6 | 10 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | አማርኛ ቋንቋን ማንበብ ክህልን መማር ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ተግባቦት ያሰፋልኛል፡፡ | 60 | 20 | 33.33 | 18 | 30 | 9 | 15 | 8 | 13.34 | 5 | 8.33 |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህልን መማር በቋንቋው የሚተላለፈውን መረጃዎች ለማግኘት ይረዳኛል፡፡ | 60 | 23 | 38.34 | 22 | 36.67 | 7 | 11.67 | 4 | 6.67 | 4 | 6.67 |

በሰንጠረዥ ሦስት የተማሪዎችን አጠቃለይ ማንበብን መማር ፍላጎትን በተመለከተ ከቀረቡ መጠይቆች በተራ ቁጥር አንድ "የአማርኛ ቋንቋ ማንበብን መማር ለእኔ አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡" በሚል ለቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች 22 (36.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (26.7%) እስማማለሁ፣ 10 (16.6%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 8 (13.3%) አልስማማም እና 4 (6.7%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ለተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማንበብን መማር አስደሳች መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር ሁለት "አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተግባቦት እና የሥራ እድል እንደሚያሰፋልኝ አውቀዋለሁ፡፡" በሚል ለቀረበው መጠይቅ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት አጠቃላይ ተማሪዎች መካከል 23 (38.3%) በጣም እስማማለሁ፣ 21 (35%) እስማማለሁ፣ 11 (18.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 3 (5%) አልስማማም፣ እንዲሁም 2 (3.34%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተግባቦት እና የሥራ እድል እንደሚያሰፋላቸው እንደሚስማሙ ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር ሦስት "በትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ የማንባብ ችሎታዬን ለማሳደግ ምቹ እድል አለኝ፡፡" በሚል ለቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ሞልተው ከመለሱ መላሾች መካከል 20 (33.33%) በጣም እስማማለሁ፣ 23 (38.33%) እስማማለሁ፣ 5 (8.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 7 (11.66%) አልስማማም እና 5 (8.34%) ተማሪዎች በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህም ማለት

ተማሪዎች በትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታቸውን ለማሳደግ ምቹ እድል እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር አራት "በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክህል መማር በጣም ያስደስተኛል፡፡" በሚል የቀረመውን መጠይቅ በትክክል ከመለሱት ተማሪዎች መካከል 26 (43፣33%) በጣም እስማማለሁ፣ 22 (36.66%) እስማማለሁ፣ 8 (13.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 2 (3.4%) አልስማማም፣ እንዲሁም 2 (3.4%) በጣም አልስማማም ያሉት ሲሆን ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂልን መማር በጣም የሚያስደስታቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

"ስለ ማንባብ ክሂል መማር ለኔ አድስ ነገር እንደማወቅ የሚያስደስት ክዋኔ ነው፡፡" በሚል በተራ ቁጥር አምስት ለቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 ተማሪዎች መካከል 21 (35%) በጣም እስማማለሁ፣ 19 (31.66%) እስማማለሁ፣ 8 (13.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 7 (11.66%) አልስማማም፣ እንዲሁም 5 (8.34%) በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ሲሆን ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎችን ስለ ማንበብ ክሂል መማር አዲስ ነገር እንደ ማወቅ የሚያስደስታቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

"የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂልን መማር ከተለያዩ መረጃ ምንጮች አንብበ ለመረዳት ምቹ እድል ይፈጥርልኛል፡፡" በማለት ለተተኳሪ ተማሪዎች በተራ ቁጥር ስድስት የቀረበውን መጠይቅ 24 (40%) በጣም እስማማለሁ፣ 18 (30%) እስማማለሁ፣ 5 (8.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 7 (11.66%) አልስማማም፣ እንዲሁም 6 (10%) በጣም አልስማማም በሚል መልሰዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል መማር ከተለያዩ መረጃ ምንጮች አንብቦ ለመረዳት ምቹ እድል የሚፈጥርላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር ሰባት "አማርኛ ቋንቋን ማንበብ ክሂልን መማር ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ተግባቦት ያሰፋልኛል፡፡" ተብሎ ለቀረበው መጥይቅ ከአጠቃላይ ተተኳሪ ተማሪዎች 20 (33.33%) በጣም እስማማለሁ፣ 18 (30%) እስማማለሁ፣ 9 (15%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 8 (13.34%) አልስማማም እና 5 (8.33%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥዋል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ማንበብ ክሂልን መማር ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ተግባቦት የሚያሰፋላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

"የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂልን መማር በቋንቋው የሚተላለፈውን መረጃዎች ለማግኘት ይረዳኛል፡፡" በማለት በተራ ቁጥር ስምንት የቀረበውን መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ሞልተው

ከመለሱት 60 ተማሪዎች መካከል 23 (38.34%) በጣም እስማማለሁ፣ 22 (36.67%) እስማማለሁ፣ 7 (11.67%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 4 (6.67%) አልስማማም፣ እንዲሁም 4 (6.67%) በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጡ መሆኑን መረጃው ያሳያል። ይህም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂልን መማር በቋንቋው የሚተላለፈውን መረጃዎች ለማግኘት እንደሚረዳቸው ያስረዳል።

እንደ አጠቃላይ በሰንጠረዥ ሦስት የአጠቃላይ ማንበብን መማር ፍላጎትን በተመለከተ የቀረቡትን 8 (ስምንት) መጠይቆች አብዛኞች ተማሪዎች መስማማታቸውን መረጃ አሳይቷል። ይህም ማለት ተማሪዎቹ የአጠቃላይ ማንበብን መማር ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል ማለት ነው።

## ሰንጠረዥ ሶስት፡- የማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች፤

| ተ/ቁ | መጠይቆች | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ ስለ ማንበብ ሳስብ ሁሌ ከፍ ያለ የጥንካሬ ስሜት ይሰማኛል። | 60 | 17 | 28.34 | 14 | 23.33 | 12 | 20 | 10 | 16.66 | 7 | 11.67 |
| 10 | ቤት በምሆንበት ወቅት ሁሌ በአማርኛ ቋንቋ ብዙ አነባለሁ። | 60 | 18 | 30 | 16 | 26.67 | 10 | 16.66 | 9 | 15 | 7 | 11.67 |
| 11 | ብዙ የማነባቸው የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት እንዲኖሩኝ | 60 | 19 | 31.676 | 15 | 25 | 13 | 21.67 | 8 | 13.33 | 5 | 8.34 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፍላጎት አለኝ። | | | | | | | | | | | |
| 12 | ካነበብኳቸው ረጅም ጊዜ ቢሆናቸውም እንኳን በቀላል የማስታውሳቸው ጉዳዮች አሉ። | 60 | 12 | 20 | 15 | 25 | 18 | 30 | 6 | 10 | 9 | 15 |
| 13 | እኔና ጓደኞቼ ባነበብናቸው መጻህፍት ዙሪያ ውይይት እናካሂዳለን። | 60 | 9 | 15 | 16 | 26.67 | 17 | 28.34 | 11 | 18.33 | 7 | 11.66 |
| 14 | ሰዎች ከሚነግሩኝ ይልቅ ራሴ ያነበብኳቸውን ጉዳዮች በበለጠ አስታውሳለሁ። | 60 | 22 | 36.67 | 20 | 33.33 | 10 | 16.66 | 6 | 10 | 2 | 3.34 |

በሰንጠረዥ አራት የተማሪዎችን ማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ በቀረቡት መጠይቆች በተራ ቁጥር ዘጠኝ "በአማርኛ ቋንቋ ስለ ማንበብ ሳስብ ሁሌ ከፍ ያለ የጥንካሬ ስሜት ይሰማኛል።" በማለት የቀረበውን መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ሞልተው ከመለሱት 60 ተማሪዎች መካከል 17(28.34%) በጣም እስማማለሁ፣ 14 (26.67%) እስማማለሁ፣ 12 (20%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 10 (16.66%) አልስማማም፣ እንዲሁም 7 (11.67%) ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ሲሆን፣ ይህም የሚያሳየው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ስለ ማንበብ ሲያስቡ ከፍ ያለስሜት እንደሚሰማቸው ያሳያል።

በተራ ቁጥር አስር "ቤት በምሆንበት ወቅት ሁሌ በአማርኛ ቋንቋ ብዙ አነባለሁ።" በሚል በቀረበው መጠይቅ መጠይቁን ከሞሉት 18 (30%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (26.67%) እስማማለሁ፣ 10 (16.66%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 9 (15%) አልስማማም፣ 7 (11.67%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ሲሆን፣ ይህም ውጤት የሚያመለክተው ከፊተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ቤት ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት በአማርኛ ቋንቋ ብዙ እንደሚያነቡ መረጃው ያመለክታል።

"ብዙ የማነባቸው የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት እንዲኖሩኝ ፍላጎት አለኝ።" ስል በተራ ቁጥር አሥራ አንድ የቀረበውን መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 ተማሪዎች መካከል 19 (31.67%) በጣም እስማማለሁ፣ 15 (25%) እስማማለሁ፣ 13 (21.67%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 8 (13.33%) አልስማማም፣ እንዲሁም 5 (8.34%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም ያሉት ሲሆን፣ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎች በአብላጫ ቁጥር ብዙ የሚያነቡት የአማርኝ ቋንቋ መጻሕፍት እንድኖሯቸው ፍላጎት እንዳላቸውን ያሳያል።

በተራ ቁጥር አሥራ ሁለት ላይ "ካነበብኳቸው ረጅም ጊዜ ቢሆናቸውም እንኳን በቀላል የማስታውሳቸው ጉዳዮች አሉ።" በማለት የቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት መካከል 12 (20%) በጣም እስማማለሁ፣ 15 (25%) እስማማለሁ፣ 18 (30%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (10%) አልስማማም፣ 9 (15%) ተማሪዎች እንዲሁም አልስማማም በማለት የመለሱት የሚያሳየው ተማሪዎች ካነበቡት ረጅም ጊዜ ብሆናቸውም እንኳን የሚያስታውሱት ጉዳይ እንዳላቸው መረጃው ያመለክታል።

"እኔና ጓደኞቼ ባነበብናቸው መጻህፍት ዙሪያ ውይይት እናካሂዳለን።" በሚል በተራ ቁጥር አሥራ ሦስት ላይ የቀረበውን መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች መካከል 9 (15%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (26.67%) እስማማለሁ፣ 17 (28.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 11 (18.33%) አልስማማም፣ እንዲሁም 7 (11.67%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል። ይህም የሚያሳየው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር ባነበቡት መጽሐፍት ዙሪያ ውይይት እንደሚያካህዱ ያሳያል።

በተራ ቁጥር አሥራ አራት እንደተገለጸው "ሰዎች ከሚነግሩኝ ይልቅ ራሴ ያነበብኳቸውን ጉዳዮች በበለጠ አስታውሳለሁ።" በማለት በቀረበው መጠይቅ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል 22 (36.67%) በጣም እስማማለሁ፣ 20 (33.33%) እስማማለሁ፣ 10 (16.66%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (10%) አልስማማም፣ እንዲሁም 2 (3.34%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም ስሉ የመለሱት ሲሆን፣ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች በአብላጫ ቁጥር ሰዎች ከሚነግሯቸው ይልቅ ራሳቸው ያነበባቸውን ጉዳዮችን በበለጠ እንደሚያስታወሱ ያመለክታል።

በአጠቃላይ በሰንጠረዥ አራት ማንበብን ፍላጎትን በተመለከተ የቀረቡትን 6 (ስድስት) መጠይቆች አብዛኞች ተማሪዎች መስማማታቸውን መረጃ አሳይቷል። ይህም ማለት ተማሪዎቹ

የማንበብ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል ማለት ነው።

## ሰንጠረዥ አራት፡- የማንበብ ችሎታን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች፤

| ተ/ቁ | መጠይቆች | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 15 | በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታዬ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። | 60 | 20 | 33.3 | 24 | 40 | 8 | 13.34 | 4 | 6.67 | 4 | 6.67 |
| 16 | አንድን በንባብ የቀረበ ጽሑፍ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢው የመግለጽ ችሎታ አለኝ ብዬ አስባለሁ። | 60 | 12 | 20 | 16 | 26.67 | 19 | 31.67 | 10 | 16.66 | 3 | 5 |
| 17 | ሳነብ የቀደመ እውቀቴን ተጠቅሜ ምንባቡን ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ። | 60 | 18 | 30 | 19 | 31.67 | 11 | 18.33 | 7 | 11.66 | 5 | 8.34 |
| 18 | ሳነብ ስለ ጽሑፉ መልዕክት በሀሳቤ ምስል በመፍጠር ለመረዳት እሞክራለሁ። | 60 | 16 | 26.67 | 18 | 30 | 13 | 21.67 | 9 | 15 | 4 | 6.66 |
| 19 | በክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት | 60 | 23 | 38.3 | 17 | 28.3 | 11 | 18.3 | 5 | 8.33 | 4 | 6.66 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወቅት በንቃት እሳተፋለሁ። | | | 3 | | 4 | | 4 | | | | |
| 20 | በማንበብ ሂደት ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት ለመገመት እሞክራለሁ። | 60 | 21 | 35 | 18 | 30 | 12 | 20 | 6 | 10 | 3 | 5 |

በሰንጠረዥ አምስት፡- የማንበብ ችሎታን በተመለከተ ስድስት መጠይቆች የቀረቡት ሲሆን፣ የተገኙ መረጃዎች ከቀረቡ መጠይቆች በተራ ቁጥር አስራ አምስት ላይ ያለውን ስንመለከት "በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታዬ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል።" በሚል የቀረበውን መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ ተማሪዎች መካከል 20 (33.33%) በጣም እስማማለሁ፣ 24 (40%) እስማማለሁ፣ 8 (13.34%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 4 (6.67%) አልስማማም፣ እንዲሁም 4 (6.67%) በጣም አልስማማም በማለት መጠይቁን የመለሱት ሲሆን፣ ይህም የሚያሳየው አብዘኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታ በጥሩ ደረጃ ላይ እንዳላቸው መረጃ ያመለክታል።

"አንድን በንባብ የቀረበ ጽሑፍ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢው የመግለጽ ችሎታ አለኝ ብዬ አስባለሁ።" በጥያቄ ቁጥር አሥራ ሳድስት ላይ በቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች መካከል 12 (20%) በጣም እስማማለሁ፣ 16 (26.67%) እስማማለሁ፣ 19 (31.67%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 10 (16.66%) አልስማማም፣ 3 (6.67%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ሲሆን፣ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች አንድን በንባብ የቀረበ ጽሑፍ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢው የመግለጽ ችሎታ እንዳላቸው ያሳያል።

በተራ ቁጥር አስራ ሰባት ላይ የቀረበው መጠይቅ ደግሞ "ሳነብ የቀደመ እውቀቴን ተጠቅሜ ምንባቡን ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ።" የሚል ሲሆን፣ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት መካከል 18 (26.66%) በጣም እስማማለሁ፣ 19 (31.67%) እስማማለሁ፣ 11 (18.33%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 7 (11.66%) አልስማማም፣ እንዲሁም 5 (8.34%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ በብዛት እንደምስማሙ ያመከለክታል።

"ሳነብ ስለ ጽሑፉ መልዕክት በሀሳቤ ምስል በመፍጠር ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡" በሚል በተራ ቁጥር አስራ ስምንት ላይ በቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች መካከል 16 (26.67%) በጣም እስማማለሁ፣ 18 (30%) እስማማለሁ፣ 13 (21.67%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 9 (15%) አልስማማም፣ 4 (6.66%) ተማሪዎች እንዲሁም በጣም አልስማማም በማለት የመለሱት ሲሆን ይህም የሚያሳየው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ስያነቡ ስለ ጽሑፉ መልዕክት በሀሳባቸው ምስል በመፍጠር ለመረዳት እንደምሞክሩ ያሳያል፡፡

በመጥይቁ ተራ ቁጥር አስራ ዘጠኝ ላይ የተገለጸው "በክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት ወቅት በንቃት እሳተፋለሁ፡፡" የሚል ሲሆን፣ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት ተማሪዎች መካከል 23 (38.33%) በጣም እሰማማለሁ፣ 17 (28.34%) እስማማለሁ፣ 11 (18.34) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 5 (8.33%) አልስማማም፣ እንዲሁም 4 (6.66%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው በአብላጫ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት ወቅት በንቃት እንደምሳተፉ መጀጃው ያመለክታል፡፡

"በማንበብ ሂደት ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት ለመገመት እሞክራለሁ፡፡" በማለት በቀረበው መጠይቅ መጠይቁን በትክክል ከሞሉት ተማሪዎች መካከል 21 (35%) በጣም እስማማለሁ፣ 18 (30%) እስማማለሁ፣ 12 (20%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 6 (10%) አልስማማም፣ አንዲሁም 3 (5%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም ብለው መልሰዋሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ አጠቃላይ ምንባቡን መልዕክት ለመገመት እንደምሞክሩ ያሳያል ማለት ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ ከላይ በቀረቡት የማንበብ ችሎታን በተመለከተ የቀረቡትን 6 (ስድስት) መጠይቆች አብዛኞች ተማሪዎች መስማማታቸውን መረጃ አሳይቷል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ የማንበብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁን ጠቅለል አድርገን ስንመለከት በሶስት ክፍሎች የቀረበው ማለትም የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የማንበብ ትምህርት ፍላጎትን፣ ሁለተኛው ክፍል የማንበብ ፍላጎት እና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የንባብ ችሎታን በተመለከተ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በጽሑፍ መጠይቅ በሦስቱም ክፍሎች መጠይቁን በትክክል ከሞሉት 60 (ስልሳ ተማሪዎች መካከል አብዘኛዎቹ ተማሪዎች በሦስቱም ክፍሎች በቀረቡት 20 (ሃያ) መጠይቆች ላይ በአብዛኛው እንደምስማሙ የተገኘው መረጃ ያመላክታል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ሲል በሦስቱም ክፍል

ተዘጋጅተው ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት አመላካች ሲሆን ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ወደ መቶኛ ተቀይሮ 73.6 ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 4.2. የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ትንተና

ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ክሂል በተግባር የማዋል ብቃትን ለመገምገም 12 (አስራ ሁለት) እውነት/ሀሰት ጥያቄዎች፣ 12 (አስራ ሁለት) የምርጫ ጥያቄዎች እና 6 (ስድስት) የባዶ ቦታ ሙሉ የሚል ጥያቄዎች በጠቅላላ 24 (ሃያ አራት) ዝግ ጥያቄዎች እና 6 (ስድስት) የክፍት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በቀላል እጣ ናሙና ከደልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል ለተመረጡ 60 (ስልሳ) ተማሪዎች ቀርቦላቸው ተፈትነዋል፡፡ ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ወደ 100% ተቀይሮ ያገኙት ውጤት በደረጃ ተከፋፍሎ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ አምስት፡- ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ክሂል በተግባር የማዋል ብቃት ለመገምገም ከተሰጠው የማንበብ ክሂል ፈተና ያገኙት ውጤት በመቶኛ፤**

| **በፈተናው ያገኙት ውጤት** | **የተማሪዎች ብዛት** | | **ማንበብ ክህል ፈተና ውጤት ደረጃ** |
|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 100-90% | 4 | 6.67% | በጣም ከፍተኛ |
| 89-75% | 20 | 33.33% | ከፍተኛ |
| 74-60% | 26 | 43.33 % | መካከለኛ |
| ከ60% በታች | 10 | 16.67% | ዝቅተኛ |
| ድምር | 60 | 100% | |

ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ክሂል ችሎታ በተግባር የማዋል ብቃት ለመገምገም የተዘጋጀውን ፈተና ከተፈተኑት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች መካከል (100-90%) 4 (6.67%)

ተማሪዎች ከፍተኛ (89-75%)፣ 20 (33.33%) ተማሪዎች መካከለኛ (74-60%)፣ እንዲሁም 10 (16.67%) ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ክሂል ውጤትን ለማወቅ የተሰጠው ፈተና አማካይ ውጤት 70.23 ሲሆን የማንበብ ክሂል ውጤታቸው መካከለኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህንን በተመለከተ Narayunaswamy (1975) የማንበብ ክህል ደረጃን ሲመድቡ ከ100-90 በጣም ከፍተኛ፣ ከ89- 75 ከፍተኛ፣ ከ74-60 መካከለኛ፣ ከ60 በታች ከሆነ ዝቅተኛ ነው በማለት ይፈርጃሉ፡፡ ከምሁሩ ብያኔ በመነሳት ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ውጤት ለማወቅ የተሰጠው የምንባብ ክሂል ፈተና ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎች ምንባብ ክሂል ውጤት ደረጃቸው **መካከለኛ** ደረጃ ላይ ሆኖ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡

### 4.2.1. የተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የንባብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ

የተማሪዎችን የንባብ ክሂል መማር ፍላጎት እና ጠምንባብ ፈተና ውጤት ለመለካት የጽሑፍ መጠይቆችና ፈተና ተዘጋጅተው በቀላል እጣ ናሙና ለተመረጡ 60 (ስልሳ) ተማሪዎች ቀርበው የተገኘው መረጃ ከፍ ብሎ ባሉት ክፍሎች ትንተና ተደርጓል፡፡ ከመረጃዎቹ በመነሳት ተዛምዷቸው በቀጣይ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ ስድስት፡- የተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ የሚያሳይ መረጃ

| ተነጻጻሪ ተላውጦዎች | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | የተዛምዶ መጠን (Corrolation) | የተዛምዶ የጉልህነት ደረጃ | የቲ-ዋጋ (t) | የነፃነት ደረጃ (df) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የማንበብ ፍላጎት ውጤት | 60 | 73.6% | 3.361% | 0.199% | 0.128% | 2.349 % | 59% |
| የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት | 60 | 70.23 % | 11.272% | | | | |

በሰንጠረዥ ሰባት የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት **73.6** ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ **70.23%** ነው፡፡ ከተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት የተገኘ መደበኛ ልይይት (Standard Deviation) **3.36%** ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት የተገኘ መደበኛ ልይይት (Standard Deviation) **11.27%** ነው፡፡ ልይይቶቹ እንደሚያሳዩት የእያንዳንዱ ተማሪ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤትም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት ውጤት ከተገኙት አማካይ ውጤቶች ብዙም ያልተራራቁ ባይሆንም የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት አመርቂ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል ተዛምዶ መኖር አለመኖርን ለማወቅ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ተሰልቶ የተዛምዷቸው መጠን **0.199** ሆኗል፡፡ ይህም  በተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ ምንባብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል **0.199%** ያህል ተዛምዶ መኖሩን ያመለክታል፡፡ በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ያለው ተዛምዶ ጉልህነት ደረጃ **0.128** ነው፡፡  ይህም የተዛምዶ መጠንን ስለካ ያለው (2009፣ 340 ) መሠረት በጣም ዘቅተኛ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡

በተማሪዎች የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና መካከል የታየው ተዛምዶ ከስህተት ነጻ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በተሠራው የአስተማማኝነት ግንኙነት መለኪያ ስሌት የ t-test ቀመር **2.349** ውጤት ተገኝቷል፡፡

## ሠንጠረዥ ሰባት፡-የፒርሰን የተዛምዶ ልኬት

| | N | ተዛምዶ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|
| **የፈተና ውጤትና የመጠይቅ ምላሽ ተዛምዶ** | 60 | 0.199 | 0.128 |

ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት እና የንባብ ፍላጎት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመለካት የምንባብ ፈተና ውጤት በመውሰድ የፍላጎት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የፒርሰን ተዛምድ ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ በስታቲስቲካዊ መረጃው መሰረት የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰልቶ (r = 0.199%), p = 0.128%) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ማለት የምንባብ ፈተና ውጤት (r = (0 .199%), p = (0.128%)፣ ይህም የንባብ ፈተና ውጤት እና በተማሪ ፍላጎት መካከል ጉልህነት ደረጃው በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መታየቱን ያሳያል፡፡

## 4.3. የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ጥናት በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ከተተኳሪ ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅና በምንባብ ፈተና የተገኘው ውጤት ትንተናም ተደርጓል፡፡ በመረጃ ትንተና በተገኘው ውጤት የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት 73.6% ሲሆን ውጤቱ ከበቂ በላይ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በሌላ መልኩ አጥኚው ባደረጉት ጥናት የተገኘው የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ውጤት 70.23% ሲሆን ውጤቱ ተቀራራቢ መሆናቸው ተመላክቷል፡፡

በሰንጠረዥ ሰባት የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል፣ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታን በተመለከተ የሚመለሱ አሥራ ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አራት አራት አማራጭ ይዘው የቀረቡ ሲሆን አብዘኛው ጥያቄዎች ለናሙና በተመረጡ 60 (ስልሳ) ተማሪዎች በአንፃራዊ መመለሳቸውን መረጃው ያስረዳል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ Ellis (1995) የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከፍተኛ ሆኖ የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን ዝቅተኛ ተነሳሽነት ዝቅተኛ ውጤትን፣ ዝቅተኛ ውጤት ደግሞ መልሶ ከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚያስከትል በሚል ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ይስማማል፡፡ እንደ ኤሊስ ድምዳሜ በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ትምህርት ፈተና አነስተኛ ውጤት ማስመዝገብ አልነበረባቸውም ማለት ነው፡፡ በጥናቱ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰሌቶ (የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት = 0.128, የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት = 0.199) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በተጠኚዎቹ ማንበብ ክህል ፈተና ውጤትና በፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስተካዊ መገመቻ ጉልህ እንዲሁም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡

የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶን ለመፈተሽ ከተማሪዎች በተሰበሰበው መረጃ የተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል በ 0.199% ያህል ተዛምዶ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡ ይህም እታጉ (2013፣52) በውጤት ማብራሪያቸው ላይ "የንባብ ፍላጎት ለንባብ ክሂል ፈተና ከፍተኛ ሚና አለው" ሲሉ ከገለጹት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሲሆን የማንበብ ፍላጎት ለተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት አስተዋጽኦ እንዳለው ያስረዳል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የምንባብ ክሂል ተዛምዶን መፈተሽ ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ ያደረገው የጥናት ንድፍ ተዛምዷዊ (Correlational) የጥናት ንድፍ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በ2016 ዓ.ም በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር ዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ለጥናቱ አመቺ እንዲሆን በቀላል የእጣ ናሙና ከዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 60 (ስልሳ) ተማሪዎች ተመርጠው መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ጥናቱን በተገቢው መስመር ለማራመድ ሁለት የምርምር መሰረታዊ መላምቶች ቀርበው በተለያዩ መረጃዎች ትንተናን በመደገፍ በቂ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ጥናቱ ያነሳቸው መሰረታዊ መላምቶች የሚከተለት ናቸው፡፡
በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል አዎንታዊ ዝምድና አለ፡፡

በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል አሉታዊ ዝምድና አለ፡፡

ከተተኳሪ ተማሪዎች የምንባብ ክሂል ፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ (SPSS Software Version 26) በመጠቀም በመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ይህንን የኮምፒውተር ሶፍትዌር በመጠቀም የተገኘውን መረጃ ለመተንተን መቶኛ፣ አማካይ ውጤት፣ መደበኛ ልይይት፣ የተዛምዶ ስሌት እና t-test አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ውጤቱ የሚያመለክት ሲሆን ፍላጎታቸውን ለመፈተሽ ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው መካከለኛ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በጥናቱ ከተተነተኑት መጠናዊ መረጃዎችና በትንተናው ከተደረሰባቸው ውጤቶች በመነሳት ይህ ጥናት ከሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ችሏል፡፡

የማንበብ ክህል መማር ፍላጎት የተማሪዎቹ የማንበብ ክህል ፈተና ውጤታቸው ጋር አውንታዊ ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

የማንበብ ክህል መማር ፍላጎት ለንባብ ክህል ውጤታቸው ጉልህ እድገት እንዲያሳይ ጠቀሜታ እንዳለው የዚህ ተግባራዊ ጥናት ግኝት አመላክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት ከማንበብ ክህል ፈተና ውጤታቸው ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምድ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የተማሪዎችን ከንባብ ጋር ያላቸውን ትስስር ለመለካት ከቀረበው ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው የተተኳሪ ተማሪዎች በሶስቱም ክፍሎች ማለትም አጠቃላይ የንባብ ትምህርት ፍላጎት፣ የንባብ ፍላጎት እና የንባብ ችሎታ በሚል በቀረበው መጠይቆች የንባብ ፍላጎታቸው መካከለኛ መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡

በ (SPSS Software Version) በተደረገው ትንተና የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት (73.6%) ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ (70.23%) መሆኑ በትናቱ ተጠቁሟል፡፡

የፍላጎት ጽንሰሀሳብ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ለአንድ የተወሰነ የትምህርት አይነት /ይዘት/ ያላቸውን የመውደድ ስሜት በመማር ተራክቦ (affective reaction) የሚገልጹበት ስነልቦናዊ አቋም ነው፡፡ (Barron & Harackiewicz, 2000)፡፡ እንደ ምሁራኑ ገለጻ ከሆነ የመማር ፍላጎት እና ውጤታማነት ተዛምዶ ተማሪው በትምህርት ሂደቱ ባሳየው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ላይ የሚመረኮዝ የፍላጎት ድምዳሜ ነው፡፡

ስለሆነም በተተኳሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል የመማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት መካከል (0.199%) ያህል ተዛምዶ መኖሩ በጥናቱ ውጤት የተመላከተ ሲሆን ይህም በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በጥናቱ የፒርሰን የተዛምድ መወሰኛ (Pearson Correlation coefficient) ተሰሌቶ (የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት = 0.128, የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት = 0.199) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በተጠኚዎቹ ማንበብ ክህል ፈተና ውጤትና በፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት

መካከል በስታቲስተካዊ መገመቻ ጉልህ እንዲሁም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት የዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸው ፍላጎት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለሚጠይቀው የጥናቱ መላምት መሠረት በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መኖሩ አንድ የጥናቱ ግኝት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2. አስተያየት

የተገኙ ውጤቶችን መነሻ በማድረግና በክለሳ ድርሳናት ፍተሻ በመደገፍ አጥኚው የሚከተሉትን አስተየየትን ለመጠቆም ችለዋል፡፡

በሰፊው እንደሚታወቀው መማሪያ ክፍል በቋንቋ የማንበብ ክህል ትምህርት ልምምዶችን ለማካሄድና ለመማር ዋንኛው ስፍራ ነው፡፡ በተለይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የቋንቋ ልምምዶች ከገሃዱ አለም ተግባቦታዊ ፍላጎቶቻቸው ጋር በተገናዘበ መንገድ የሚቀርቡ ከሆነ የተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ ማንበብ ክህል የመማር ፍላጎትና ውጤታማ የመሆን ተነሳሽነት እንሚደሻሻል ይህ ተግባራዊ ጥናት ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸው ከፍተኛ የማንበብ ፍላጎት እንዲኖራቸው የተለያዩ የንባብ ዘዴዎችን የመጠቀም ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ቢያደርጓቸው የተሻለ ነው፡፡

በICDR (2009) እንደቀረበው፣ በችግር ላይ ተመስርቶ ክፍተትን ለመሙላት የሚቀርብ ብሎም ውጤቶችንና የመፍትሄ አማራጮችን ለመጠቆም የሚረዳ ክንውን ጠቃሚ የተማሪዎች የመማር ችግሮችን ማቃለያው ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ትምህርት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ውጤቱ ወይም መፍትሄው የችግሩን ክፍተት መሙላትን ታሳቢ አድርጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ይህ ሂደት ‹‹ውጤት ትንተና›› (means-ends analysis) ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህም የተነሳ ችግር ፈቺ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ትምህርት ተማሪዎቹ በሚገኙበት የክፍል ደረጃ ባሏቸው የእውቀት ክፍተት ላይ ተመስርተው የሚፈለገውን አዲስ እውቀትና ክህሎት ለመጨበጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህል መማሪያ አውድ ላለባቸው ጉልህ የክህሎት ችግሮች ቅድሚያ በመስጠት ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት ቢጥሩ ተማሪዎቹ ጉልህ ችግሮቻቸው በመቃለላቸው መጠን ሌሎች ችግሮችን እያቃለሉ ለመማር ልምድ ያገኛሉ፡፡ ሁለተኛ ቋንቋው የማንበብ ክህል የመማር ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ በራስ መተማመን ያዳብራሉ፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎታቸውን ለማሻሻል ለተማርዎች

የሚታይባቸውን/ያለባቸውን ችግሮችን በመለየት ከክፍል ደረጃቸው ጋር የተመጣጠነ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የማንበብ ክሂል ትምህርት ቢያስተምሯቸው የተሸለ ይሆናል፡፡

በቋንቋ መማሪያ አውድ የሚደረስባቸው እውነተኛ /ተጨባጭ/ የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት ግቦችን ማስቀመጥና እነዚህን ግቦች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመጨበጥ የሚደረግ ትምህርታዊ እንቅስቃሴ በተማሪዎች አስተሳሰብ ውስጥ የመማር ፍላጎትን ለማስረጽ ቁልፍ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን በየደረጃው ተማሪዎቹ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ክህል መማርን በአሳታፊ መንገድ ተወያይተው እንዲያስቀምጡና እነዚህን ግቦች መጨበጥ አለመጨበጣቸውን በግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ እየገመገሙ እንዲማሩ ቢያደርጉ በሁለተኛ ቋንቋ ማንበብን መማር ፍላጎት የተሻለ እና ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው እንዲጎለብት በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ የተለያዩ ጽሑፎችን እያነበቡ የማንበብ ልምዳቸውን ቢያጎለብቱ፣

በመደጋገፍ መማር ተማሪዎች ትንንሽ ቡድኖችን መስርተው እርስ በርስ በመማማር የራሳቸውን መረዳት መጠን ከፍ ለማድረግም ሆነ ሌሎች እንዲረዱ ለማገዝ አብረው የሚሰሩበት አውድ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ድግግፋዊ መማር በአዎንታዊ አቻዊ ግንኙነትና እርስ በእርስ መደጋገፍ ከፍ ወዳለው የመማማር ውጤታማነት ለመድረስ የሚያግዝ ብልሃት ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል መማሪያ አውድ ላይ በመደጋገፍ የመማር ስሌቶችን ቢያጠናክሩ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎትን በመጨመርና ውጤታቸውን እንደምጨምር እንዲሁም ተማሪዎች የተሻለ ተግባቦታዊ ፍላጎት እና ችሎታ ሊያዳብሩ እንደሚችሉ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

## መደምደሚያ

ከፍ ሲል በተናጥል የተጠቀሱትን የጥናቱን ውጤቶች መሠረት ማድረግ ጥናቱ ከሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ደርሷል፡፡

ሀ. ተማሪዎች ፍላጎት እንዳላቸውና ደረጃውም ከፍ ያለ እንደሆነ ታይቷል፡፡

ለ. ተማሪዎች ያላቸው ፍላጎትና የማንበብ የትምህርት ፈተና ውጤታቸው በስታቲስቲክስ በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


በረከት ሁሴን፡፡ (2010)፡፡ በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ቤት በአማርኛ ኢ-አፍፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ፡፡ ለአማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ብርሀን ሲራጅ፡፡ (2003)፡፡ "የንባብ ልምድና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በውቅሮ፤ በነጋሽና አጉላዕ ሁለተኛደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት፡፡" ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1986)፡፡ አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር፡፡ አድስ አበባ፣

አለም እሸቱ፡፡ (1997)፡፡ መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡ አድስ አበባ ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋካልቲ፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (2001)፡፡ "የወጣቶች የንባብ ልምድ ፍተሸ በአድስ አበባ ወጣቶች መነሻነት" መድበለ ጉባኤ 61-69፡፡

አለምነሽ የኔነሁ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ አዊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ያሏቸው ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሐፍ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባህር ዳር፡፡

የኔሰው ደሴ፡፡ (1990)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ ሞዳል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ፡፡ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ኦፍ አርትስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡

ይድነቃቸው ገረመው፡፡ (2013)፡፡ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ግለብቃት እምነት ተዛምዶ፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተተኳሪነት፤ ለአማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ስመኝ፡ አባሁና፡፡ (2002) ፡፡ በሁሩሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለቸዉ ተነሳሽነት፡፡ለመጀመርያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ጅማ ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)

አለም እሼቱ፡፡(1994)፡፡ መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አጻጻፍ ፡፡ አዲስ አበባ የንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዘሪቱ አስፋዉ፡፡ (2003) ፡፡በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ፡፡ለሁለተኛድግሪ ማሟያነት የቀረበ ፅሁፍ፡ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡ (2009)፡፡ "ኢትዮጵያዉያን እና ንባብ፡፡ አዲስ አበባ፤

ክፍሌ ሰበረዉ፡፡ (2002)፡፡ አፋቸዉን በጉሙዝኛ ቋንቋን የፈቱ የ9ኛ ከፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉጤት ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

እባቡ‹ንጉሴ፡፡(2000)፡፡ በሰቃ 2ኛ፡፡ደረጃትምህርት/ቤት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሰቲ፡፡(ድ.ማ.ፅ)፡ ፡ያልታተመ፡

ጀማል ባዲ (2001) ፡፡በሴሩ አባስ 2ኛ ደረጃትምህርትቤት የ9ኛ ክፍልተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት ትንተና በጅማ ዩኒቨርሰቲ፡፡ያልታተመ፡፡

ያለዉ እንዳወቀ፡፡ (1998) የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡

Bachman (2010). Language assessemente in practice oxford university press.

Bainbridge, C. (2014). High Achiever: Gifted Children Categories.

Barron, K. E., & Harackiewicz, ]. M. (2000). Achievement goals and optimal motivation: A multiple goals approach. In C. Sansone & ]. M. Harackiewicz (Eds.), Intrinsic and extrinsic motivation-. The search for optimal motivation and performance (pp. 231-256). New York: Academic Press.

Brown H.D. (1994) principles of language learning and teaching (3rd Ed) USA.

Sanfarancisco state university.

Brown, H.D. (2000). Principles of Language Learning and Teaching. (4th ed.). USA: Longman Inc.

Brown.H. D, (2000), principles of language learning and teaching (2nd Ed) USA.longmanInc.

Dorneeyei, Z. (2001) Teaching & Researching Motivation London education limited.

Eidswick, J. (2010). Interest and prior knowledge in second language reading comprehension. JALT Journal, 32 (2), 149—168.

Elis.R. (1997) second language Acquisition oxford; oxford university press.

Elliot, J.G.etal (2005) motivation, Engagement and education performance.interbational Perspective on the contexts for learning New York: pellagara.

Ellis, R. (1997). Sceond Language Acquisition. Oxford: Oxford University Press.

Freeman, D.L. and Long, M.H. (1992) An introducation to second language aequisition research (3rd edit) New York Longman group UK lit.

Gardener R.C.(1982) language attitude and language learning in Ryan E.B(Ed),attitudesTowards Language variation:social and applied contex.Britain Edward Arnold.

Gardner.R.C (1985) social psycology and second language learning.therolof attitudesand motivation. London: Arnold.

Gardner.R.C (2003) <<Attitudes, Motivation and second language learning. Ameta .Analysis of studies.

Gardner.R.C.(2004), Attitude motivation Test battery. International AMTB Research Project. The university of westernontario, Canada Retrieved April, 2011.

Gu, Yueguo. (2010). English language Teaching Methodology. Beijing: Foreign

Language Teaching and Research Press.
Guo, Z. F., and Zhang, D. Q. (2012). The main reason of learning weariness in primary school students: the overburden of study load. Res. Basic Edu. 18, 3—5.
Gutherie, I. T., & Cox, K. E. (2011). Classroom conditions for motivation and engagement in reading. In K. A. Renninger, & S. E. Wade (Guest Eds.), Student interest and engagement. Educational Psychology Review, 13 (3), pp. 283-3.
Hamilin, E. (1996). Oxford advanced Learners' Dicticreny (5th ed). New York University press.
ICDR. (2009). Teacher Roles in the Learner-Centered Classroom. ELT Journal. Vol. 47,No. 1.
MOE (2004). Education and Training policy, Addis Ababa; MOE/NOE (National Organization for Examinations) Dec 2004, Ethiopian Second National Learning assessments of grade 4 students and grade 8 students. ESDP I to IV, 2000-2011, MOE, Addis Ababa.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- ስለ ጽሑፍ መጠይቅ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ**
**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል**
**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**
**ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ**

**ውድ ተማሪዎች!**

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በዳውሮ ዞን ገሳ ከተማ አስተዳደር በዳልቫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዳውሮኛ ቋንቋ አፊቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ ለመፈተሽ ነው፡፡ መጠይቁ ባለ አምስት የመልስ አማራጮች አሉት፡፡ ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አቋም የለኝም፣ አልስማማም እና ፈጽሞ አልስማማም ከሚሉ የመልስ አማራጮች መካከል ለአንተ/ቺ/ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በየጥያቄዎቹ አንጻር በየሳጥኑ ውስጥ የ‹‹X›› ምልክት በማድረግ መጠይቁን ሞልታችሁ ጨርሱ፡፡ በቅድሚያ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ትብብራችሁን ስላሳያችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**መግለጫ፡-**

በጣም እስማማለሁ (5)
እስማማለሁ (4)
መወሰን አልችልም (3)
አልስማማም (2)
በጣም አልስማማም (1)

**የትውውቅ ክፍል፤**

የትምህርት ቤቱ ሥም:------------------------------------------ የክፍል ደረጃ:----------------

ፆታ:- ------------- ዕድሜ:- ------------- ቀን:----------------------- መለያ ቁጥር---------------

| ተራቁጥር | ጥያቄ | | የምላሽ አሰጣጥ አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አቋም የለኝም | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም |
| | **አጠቃላይ ፍላጎትን በተመለከተ** | | | | | | |
| 1 | አማርኛ ቋንቋ መማር ለእኔ አስደሳች ክንዋኔ ነው፡፡ | 60 | | | | | |
| 2 | አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተግባቦት እና የሥራ እድል እንደሚያስፋልኝ አውቀዋለሁ፡፡ | 60 | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | በትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ችሎታዬን ለማሳደግ ምቹ እድል አለኝ፡፡ | 60<br>60 | | | | | |
| 4 | አማርኛ ቋንቋን መማር በጣም ያስደስተኛል፡፡ | 60 | | | | | |
| 5 | አማርኛ ቋንቋን መማር ለኔ እንደ አድስ<br>ነገር እንደማወቅ የሚያስደስት ክዋኔ ነው፡፡ | 60 | | | | | |
| 6 | አማርኛ ቋንቋን መማር ከተለያዩ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ምቹ እድል ይፈጥርላኛል፡፡ | 60 | | | | | |
| 7 | አማርኛ ቋንቋን መማር ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ተግባቦት ያሰፋልኛል፡፡ | 60 | | | | | |
| 8 | አማርኛ ቋንቋን መማር | 60 | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በቋንቋው የሚተላለፈውን መረጃዎች ለማግኘት ይረዳኛል፡፡ | | | | | | |

## የማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ

| ተ/ቁ | መጠይቆች | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን አልችልም | አልስማማም | በጣም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ ስለ ማንበብ ሳስብ ሁሌ ከፍ ያለ የጥንካሬ ስሜት ይሰማኛል፡፡ | | | | | | |
| 10 | ቤት በምሆንበት ወቅት ሁሌ በአማርኛ ቋንቋ ብዙ አነባለሁ፡፡ | | | | | | |
| 11 | ብዙ የማነባቸው የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት እንዲኖሩኝ ፍላጎት አለኝ፡፡ | | | | | | |
| 12 | ካነበብኳቸው ረጅም ጊዜ ቢሆናቸውም እንኳን በቀላል የማስታውሳቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | እኔና ጓደኞቼ ባነበብናቸው መጻህፍት ዙሪያ ውይይት እናካሂዳለን፡፡ | | | | | | |
| 14 | ሰዎች ከሚነግሩኝ ይልቅ ራሴ ያነበብኳቸውን ጉዳዮች በበለጠ አስታውሳለሁ፡፡ | | | | | | |

**የማንበብ ችሎታን በተመለከተ**

| ተ/ቁ | መጠይቆች | የናሙና ቁጥር | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 15 | በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታዬ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ | | | | | | | | | | | |
| 16 | አንድን በንባብ የቀረበ ጽሑፍ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢው የመግለጽ ችሎታ አለኝ ብዬ አስባለሁ፡፡ | 60 | | | | | | | | | | |
| 17 | ሳነብ የቀደመ እውቀቴን ተጠቅሜ ምንባቡን ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ | | | | | | | | | | | |
| 18 | ሳነብ ስለ ጽሑፉ መልዕክት | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በሀሳቤ ምስል በመፍጠር ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡ | | | | | | |
| 19 | በክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት ወቅት በንቃት እሳተፋለሁ፡፡ | 60 | | | | | |
| 20 | በማንበብ ሂደት ዘዴ በተሞላበት ሁኔታ አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት ለመገመት እሞክራለሁ፡፡ | 60 | | | | | |

**(ምንጭ፡- ከ**National Research Council (2003) **እና** Schiefele (2008) **ለዚህ ጥናት እንዲስማማ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)**

# አባሪ ሁለት

## ስለ ማንበብ ክሂል ፈተና

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስ እና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ**

**አማርኛ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መረሃ ግብር**

**ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ፈተና**

**የትምህርት ቤቱ ስም-----------------------------------------**

**የተፈታኙ መለያ ኮድ፡- -------------**

**የተፈቀደዉ ሰዓት 1፡30**

**በፈተናው ላይ ስም መጻፍ አይፈቀድም**

**ምንባብ አንድ**

**ቅርስና የቅርስ አይነቶች**

ቅርስ በውስጡ ካካተው ከፍተኛ እሴት አኳያ በተለያዩ አለም አቀፋዊ እና አገር አቀፋዊ መስፈርቶች፣ ማለትም ከእድሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅዬነቱ... ወዘተ አኳያ በተለያዩ መመዘኛዎች የተመረጠ የተፈጥሮ ስጦታ እና ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት ወይም ሁለቱንም በጣምራ (የተፈጥሮ እና ባህላዊ ቅርስን ያያዘ) ያካተተ ነው፡፡ ቅርስ ተፈጥሮ የለገሰንን እና የሰው ልጅ በኖረበት ዘመን ያከማቻቸውን የፈጠራ ውጤቶችን ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ቁጥሩ እና አይነቱ እጅግ ብዙ ነው፡፡ ቅርስን በአራት አይነት ከፍለን ማየት ይቻላል፡፡

**አንደኛ፡-** ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርስ ሲባል አብዛኞቻችን የምናስበው ከባህል ጋር በተገናዘበ መልኩ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅርስ የተመረጡ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና የሰው ልጅን የፈጠራ ውጤቶችን ወይም የሁለቱንም ጥምረት የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

የባህል ቅርስ የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶችን ማለትም ሀውልቶችን፣ ህንፃዎችን፣ ዋሻዎችን፣ በድንጋይ እና በብራና… ወዘተ. በመሳሰሉት ላይ የተጻፉ ወይም የተቀረጹ ጽሁፎችን፣ ቅርጻ ቅርጾችን፣ አልባሳቶችን፣ እምነቶችን፣ ወጎችን፣ ስርአቶችን… ወዘተ ሁሉ ያካትታል፡፡ የተፈጥሮ ቅርስ ደግሞ በላቀ ጠቀሜታቸው የተመረጡ ማራኪ እና ውብ የሆኑ ደኖችን፣ ሀይቆችን፣ ዋሻዎችን፣ ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የእንስሳት መጠለያዎችን፣ በአጠቃላይ ህይወት ያለቸውን እና የሌላቸውን ፍጡሮች እና እነርሱም የሚገኙባቸውን ቦታዎች ሁሉ ያካትታል፡፡

**ሁለተኛ፡-** የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ ካለው ጠቀሜታ አንጻር የአለም ቅርስ እና ብሔራዊ ቅርስ በሚል በሁለት ይከፈላል፡፡ አንድ ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያካተተ ቅርስ) የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት ባወጣው መመዘኛ መሰረት በውስጡ የላቀ አለም አቀፍ እሴት ካለው፣ የአለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በአለም ቅርስነት ተመዝግቦ የአለም ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ ብሔራዊ ቅርስን በተመለከተ ደግሞ እያንዳንዱ መንግስት ባወጣው መመዘኛ መሰረት ማንኛውም ብሔራዊ እሴት ያለው ቅርስ (የባህል፣ የተፈጥሮ እና ሁለቱንም በጣምራ ያከተተ ቅርስ) ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ከሆነ በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቦ ብሔራዊ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡ በዩኔስኮ የውሳኔ ሰነድ መሰረት የአለም የባህል ቅርስ የሚባሉት ሀውልቶች፣ ሕንጻዎች፣ ከታሪክ፣ ከስነ ጥበብ እና ከሳይንስ አንጻር የላቀ አለም አቀፍ እሴት ያላቸው ቦታዎች፣ የተፈጥሮ እና የሰው ስራዎችን በአንድ ላይ ያጣመሩ የቁፋሮ ቦታዎችንም ያካትታል፡፡

**ሦስተኛ፡-** ተንቀሳቃሽ እና የማይነቀሳቀስ ቅርስ ከአይነቱ ከተፈጥሮው እና ከመጠኑ አንጻር ቅርስ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ተንቀሳቃሽ የሚባለው በቀላል ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የሚችል የቅርስ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በቅርስነት የተመዘገቡ በብራና ላይ የተጻፉ ጽሁፎች፣ አልባሳት በተለያዩ ቁሳቁሶች (ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከሸክላ ከድንጋይ ከወርቅ… ወዘተ) የተሰሩ እቃዎች እና ቅርፃ ቅርፆች መጠናቸው አነስተኛ የሆነ በቁፋሮ የተገኙ ጥንታዊ የመገልገያ እቃዎች… ወዘተ በቀላል ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊወሰዱ ስለሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የማይንቀሳቀስ የሚባለው በቀላል ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት፣ ታሪካዊ የሀረር ከተማ ጀጎል ግንብ፣ የአል-ነጃሺ መስጊድ፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ… ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡ በአለም ቅርስነትም የተመዘገቡ

ናቸው። አፈጣጠራቸው ከግዝፈታቸው እና ከሚገኙባቸው ቦታዎች አኳያ በቀላል ለማንቀሳቀስ አይቻልም።

**አራተኛ፡-** ተጨባጭ እና ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሽተው… ወዘተ በአጠቃላይ በሁሉም ስሜት ህዋሳቶቻችን ልንገነዘበው የምንችለው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃል። ለምሳሌ፡- ሀውልቶች፣ ህንጻዎች ዋሻዎች፣ መጻህፍት፣ የተለያዩ ቅርሳ ቅርሶች፣ አልባሳት… ወዘተ ተጨባጭ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ። ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሽተው… ወዘተ የማንችለው ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃል።

ወጎች፣ ተረቶች፣ ስርአቶች፣ ማራኪ እይታዎች፣ ባህላዊ እና ሃማኖታዊ ስርአቶች ወዘተ ቁሶች አይደሉም። በውስጣቸው ግን መንፈሳችንን የሚያነሳሱ፣ የአእምሮ እርካታንም የሚሰጡን በርካታ እሴቶች አሏቸው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማወቅን መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መደሰትን… ወዘተ፣ ሁሉ ይፈልጋል። ፍላጎቶች ሁሉ ግን በቁሳዊ ፍላጎቶች ብቻ ሊረኩ ከቶውንም አይቻላቸውም። ተጨባጭ ከሆኑት ወይም ከቁሳዊ ፍላጎቶቹ በተጨማሪ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ያልሆኑ ፍላጎቶችም አሉት። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ። በአጠቃላይ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የሰውን ልጅ አኗኗር፣ ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና ወግ እና ስርአትን የሚያንፀባርቁ የዘመን አሻራዎች ናቸው።

**ምንጭ፡- ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስቴዲስ (2004) ተሻሽሎ የተወሰደ**

***መመሪያ አንድ፡- ከዚህ ቀትሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን ሀሳብ እውነት ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ።***

1. በዩኒስኮ የውሳኔ ሰነድ መሰረት የአለም የባህል ቅርስ የሚባለው የአለም ህዝቦች ሊያደንቁት፣ ሊማሩበት እና ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ነው።
2. ቅርስ ተፈጥሮ <u>የለገሰንና</u> የፈጠራ ውጤቶችን ያጠቃልላል። የተሰመረበት ቃል ፍቺ የሰጠንን ማለት ነው።
3. በምንባቡ መሠረት የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት ከማይንቀሳቀስ ቅርስ አንዱ ነው።
4. ለአንድ ሀገር የቅርስ ጥቅሙ የሀገሪቱን የዓመቱን በጀት መሸፈን ነው።

5. በምንባቡ መሠረት ተጨባጭ ቅርስ ያልሆነው ባህላዊ ክብረ በዓል ነው፡፡
6. የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የሰውን ልጅ አኗኗር፣ ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና ወግ እና ስርአትን የሚያንፀባርቁ የዘመን አሻራዎች ናቸው፡፡
7. ልናየው፣ ልንዳስሰው፣ ልናሸተው... ወዘተ የማንችለው ነገር ግን የውስጥ ስሜታችንን የሚያረካ ቅርስ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃል፡፡
8. የሚንቀሳቀስ ቅርስ የሚባለው በቀላሉ ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊወሰድ የማይችል የቅርስ አይነት ነው፡፡
9. የባህል ቅርስ የሚባለው የተመረጡ የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶችን ያጠቃልላል፡፡
10. ቁሳዊ ያልሆኑና መንፈሳችንን በማነሳሳት የአእምሮ እርካታን የሚሰጡን ነገሮች በቅርስነት ሲመዘገቡ ተጨባጭ ያልሆነ ቅርስ በመባል ይታወቃሉ፡፡
11. የአል-ነጃሺ መስጊድ እና የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ በአለም ቅርስነት አልተመዘገበም፡፡
12. በዩኔስኮ የውሳኔ ሰነድ መሰረት የአለም የባህል ቅርስ የሚባሉት ሀውልቶች እና ሕንጻዎች ብቻ ናቸው፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከቀረበው አማራጮች መርጠህ/ሽ በተሰተው መልስ ማስቀመጫ ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡**

13.ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርስ ስንል ምን-------------ማለት፡፡

ሀ. ተፈጥሮ እና የፈጠራ ውጤቶች ለ. ዓለም አቀፍ እሴት ያላቸው

ሐ. በዩኔስኮ የተመዘገቡ ማለታችን ነው መ. ብሔራዊ ቅርስ

14.በምንባቡ አንቀጽ አምስት ላይ "ተንቀሳቃሽ" ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ለ. የማይዳሰስ

ሐ. ግዙፍ በዐይን የሚታይ መ. የሚዳሰስ

15.ተጨባጭ ቅርስ ማለት--------------ማለት ነው፡፡

ሀ. የማይንቀሳቀስ ለ. የሚዳሰስ፣ የምታይ

ሐ. እምነቶች፣ ወጎች መ. ባህሎች

16.ተጨባጭ ባልሆነ ቅርስ ውስጥ የሚካተተው ቀጥለው ከቀረቡት ውስት የቱ ነው?

ሀ. አልባሳት ለ. የተለያዩ እምነታዊ ስርዓቶች

ሐ. ብሔራዊ ፓርኮች መ. ሀውልቶችና ቅርጻቅርጾች

17.በምንባቡ በመጀመሪያው አንቀጽ "ሲወርድ ሲዋረድ" የሚለውን ሐረግ የሚተካው ----- ነው፡፡

ሀ. ከዘመን ዘመን እየተለወጠ ለ. ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ

ሐ. ያለው ክብር ሲቀነስ መ. ባለ ዘመን ሁሉ

18.በምንባቡ መሰረት ቅርስ የሚለውን የማይገልጸው የቱ ነው?

ሀ. በእድሜ አንጋፋ ከሆነ ማንኛውም ቁስ ቅርስ ልባል ይችላል፡፡

ለ. የተፈጥሮ ስጦታ እና ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ቅርስ ይባላል፡፡

ሐ. ቅርስ ከእዳሜው፣ ከውበቱ፣ ከጠቀሜታው፣ ከብርቅየነቱ አንጻር ልታይ ይችላል፡፡

መ. የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ቅርስ ልባል ይችላል፡፡

19. በምንባቡ ‹‹ብርቅ›› የሚለው ቃል ትርጉም............................ማለት ነው፡፡

ሀ. አዲስ ለ. ነባር ሐ. አስገራሚ መ. የሚያብለጨልጭ

20.በምንባቡ መሰረት በቁፋሮ የሚገኙ ጥንታዊ የመገልገያ እቃዎች ...............ናቸው፡፡

ሀ. ተጨባጭ ያልሆኑ ቅርሶች ለ. ተጨባጭ ቅርሶች

ሐ. ተፈጥሯዊ እና ተጨባጭ ቅርሶች መ. የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች

21. የአለም ቅርስ የሚባሉት ምን መስፈርት ያሟሉ ናቸው?

ሀ. አብረቅራቂ እና ትልቅ ከሆኑ

ለ. በቁፋሮ ከተገኙ

ሐ. በቆዳ እና በድንጋይ ላይ ከተጻፉ

መ. በውስጣቸው ከፍተኛ እሴት ካሏቸው

22. በምንባቡ መሰረት እሴት የሚለው ቃል ፊቺ .....................ነው፡፡

ሀ. ዋጋ ለ. ቀረጥ ሐ. ውበት መ. መጠን

23. ከሚከተለት መካከል ቅርስ ያልሆነውን ለይ/ዩ፡፡

ሀ. ቅርጻ ቅርጾች፣ አልባሳት፣ እምነቶች፣ ወጎችና ባህላዊ ስርአቶች

ለ. ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ስርአቶች

ሐ. የላልበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትና የአል-ነጃሺ መስጊድ

መ/ መልሱ አልተሰጠም፡፡

24.ፀሐፊው ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው?

ሀ. ቅርሶች የሐገርና የአለም ሐብት መሆናቸውን

ለ. የሐገራችን ቅርስ እየተመዘበረ መሆኑ

ሐ. ቅርሶች አይነታቸው ብዙ በመሆኑ መለየት አስቸጋሪ መሆኑን

መ. ቅርሶች ዋጋቸው በጣም ውድ መሆኑን

***መመሪያ ሦስት፤ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከምንባቡ በመፈለግ ባዶ ቦታውን ሙሉ።***

25. በምንባቡ ውስጥ ፀሐፊው ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ------- ነው?
26. በምንባቡ መሰረት "እሴት" የሚለው ቃል ፍቺ .....................ነው።
27. በምንባቡ አውድ ‹‹ማድነቅ›› የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው ------ ነው።
28. በምንባቡ መሰረት ብራና ማለት...................... ነው።
29. ጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ የቅርስ አከፋፈል ........................ ይባላል።
30. በምንባቡ መሰረት ‹‹አሻራ›› የሚለው ቃል ፊቺ .......................ነው።

# አባሪ ሦስት

## በኮድ ሽት የተመዘገበ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት

### የጾታ ውክልና (ወንድ=1፣ ሴት=2)

| መ/ቁ | ፆታ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር ከመቶ |
| 1 | 1 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 80 |
| 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 5 | 3 | 2 | 5 | 4 | 73 |
| 3 | 2 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 1 | 5 | 71 |
| 4 | 2 | 3 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 1 | 71 |
| 5 | 1 | 5 | 3 | 2 | 5 | 1 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 3 | 2 | 4 | 5 | 69 |
| 6 | 1 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 4 | 3 | 3 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 2 | 71 |
| 7 | 1 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 3 | 2 | 5 | 72 |
| 8 | 2 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 73 |
| 9 | 1 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 1 | 5 | 3 | 68 |
| 10 | 2 | 3 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 5 | 75 |
| 11 | 2 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 1 | 5 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 5 | 66 |
| 12 | 1 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 1 | 4 | 2 | 5 | 2 | 71 |
| 13 | 1 | 1 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 73 |
| 14 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 3 | 72 |
| 15 | 2 | 2 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 75 |
| 16 | 2 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 5 | 71 |
| 17 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 1 | 74 |
| 18 | 2 | 5 | 3 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 75 |
| 19 | 1 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 2 | 72 |
| 20 | 1 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 73 |
| 21 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 74 |
| 22 | 1 | 4 | 1 | 5 | 5 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 2 | 4 | 2 | 5 | 4 | 71 |
| 23 | 1 | 2 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 4 | 3 | 1 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 72 |
| 24 | 2 | 5 | 5 | 1 | 5 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 77 |
| 25 | 1 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 79 |
| 26 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 2 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 80 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | 2 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 1 | 4 | 3 | 74 |
| 28 | 1 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 3 | 5 | 3 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 78 |
| 29 | 1 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 4 | 3 | 4 | 72 |
| 30 | 2 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 3 | 75 |
| 31 | 2 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 5 | 77 |
| 32 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 77 |
| 33 | 1 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 73 |
| 34 | 2 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 4 | 5 | 76 |
| 35 | 1 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 73 |
| 36 | 1 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 | 5 | 2 | 76 |
| 37 | 2 | 2 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 76 |
| 38 | 1 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 78 |
| 39 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 74 |
| 40 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 76 |
| 41 | 1 | 1 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 79 |
| 42 | 1 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 72 |
| 43 | 2 | 2 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 76 |
| 44 | 1 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 2 | 5 | 71 |
| 45 | 1 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 4 | 2 | 4 | 1 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 5 | 2 | 70 |
| 46 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 78 |
| 47 | 1 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 75 |
| 48 | 1 | 1 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 5 | 3 | 5 | 70 |
| 49 | 2 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 72 |
| 50 | 2 | 4 | 5 | 1 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 75 |
| 51 | 1 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 72 |
| 52 | 1 | 5 | 2 | 2 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 | 3 | 1 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 69 |
| 53 | 2 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 2 | 4 | 1 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 72 |
| 54 | 1 | 5 | 2 | 4 | 5 | 3 | 5 | 2 | 5 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 72 |
| 55 | 1 | 1 | 5 | 5 | 3 | 5 | 1 | 5 | 4 | 3 | 1 | 5 | 3 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 70 |
| 56 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 4 | 1 | 4 | 2 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 69 |
| 57 | 1 | 3 | 5 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 3 | 5 | 4 | 3 | 3 | 5 | 2 | 67 |
| 58 | 1 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 76 |
| 59 | 2 | 2 | 5 | 5 | 3 | 5 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 3 | 2 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 76 |
| 60 | 2 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 82 |
| አማካይ ውጤት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | 73.6 |

# አባሪ አራት

## የንባብ ክሂል ውጤት

| መ/ቁጥር | ጾታ | ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 1 | 70 |
| 2 | 1 | 53 |
| 3 | 2 | 70 |
| 4 | 2 | 67 |
| 5 | 1 | 67 |
| 6 | 1 | 63 |
| 7 | 1 | 50 |
| 8 | 2 | 70 |
| 9 | 1 | 53 |
| 10 | 2 | 77 |
| 11 | 2 | 77 |
| 12 | 1 | 77 |
| 13 | 1 | 83 |
| 14 | 1 | 67 |
| 15 | 2 | 57 |
| 16 | 2 | 60 |
| 17 | 1 | 50 |
| 18 | 2 | 73 |
| 19 | 1 | 80 |
| 20 | 1 | 77 |
| 21 | 2 | 80 |
| 22 | 1 | 70 |
| 23 | 1 | 70 |
| 24 | 2 | 67 |
| 25 | 1 | 83 |

| | | |
|---|---|---|
| 26 | 1 | 77 |
| 27 | 2 | 63 |
| 28 | 1 | 63 |
| 29 | 1 | 83 |
| 30 | 2 | 83 |
| 31 | 2 | 80 |
| 32 | 1 | 53 |
| 33 | 1 | 77 |
| 34 | 2 | 90 |
| 35 | 1 | 63 |
| 36 | 1 | 93 |
| 37 | 2 | 73 |
| 38 | 1 | 90 |
| 39 | 1 | 70 |
| 40 | 2 | 83 |
| 41 | 1 | 70 |
| 42 | 1 | 67 |
| 43 | 2 | 70 |
| 44 | 1 | 70 |
| 45 | 1 | 60 |
| 46 | 2 | 53 |
| 47 | 1 | 57 |
| 48 | 1 | 67 |
| 49 | 2 | 67 |
| 50 | 2 | 67 |
| 51 | 1 | 60 |
| 52 | 1 | 67 |
| 53 | 2 | 80 |
| 54 | 1 | 97 |
| 55 | 1 | 77 |

| | | |
|---|---|---|
| 56 | 2 | 77 |
| 57 | 1 | 53 |
| 58 | 1 | 53 |
| 59 | 2 | 63 |
| 60 | 2 | 87 |
| ኣማካይ ውጤት | | 70.23 |

## አባሪ አምስት

### የማንበብ ፍላጎትና ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ፤

| መ/ቁ | ፆታ | ትምህርት ቤት ሥም | ዕድሜ | ክፍል | የማንበብ ፍላጎት ውጤት | ማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 80 | 70 |
| 2 | Male | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 73 | 53 |
| 3 | Female | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 71 | 70 |
| 4 | Female | ዳልቫ | 19 | 9ኛ | 71 | 67 |
| 5 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 69 | 67 |
| 6 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 71 | 63 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 72 | 50 |
| 8 | Female | ዳልቫ | 19 | 9ኛ | 73 | 70 |
| 9 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 68 | 53 |
| 10 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 75 | 77 |
| 11 | Female | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 66 | 77 |
| 12 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 71 | 77 |
| 13 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 73 | 83 |
| 14 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 72 | 67 |
| 15 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 75 | 57 |
| 16 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 71 | 60 |
| | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | Male | ዳልባ | 16 | 9ኛ | 74 | 50 |
| 18 | Female | ዳልባ | 16 | 9ኛ | 75 | 73 |
| 19 | Male | ዳልባ | 18 | 9ኛ | 72 | 80 |
| 20 | Male | ዳልባ | 19 | 9ኛ | 73 | 77 |
| 21 | Female | ዳልባ | 20 | 9ኛ | 74 | 80 |
| 22 | Male | ዳልባ | 17 | 9ኛ | 71 | 70 |
| 23 | Male | ዳልባ | 17 | 9ኛ | 72 | 70 |
| 24 | Female | ዳልባ | 18 | 9ኛ | 77 | 67 |
| 25 | Male | ዳልባ | 16 | 9ኛ | 79 | 83 |
| 26 | Male | ዳልባ | 20 | 9ኛ | 80 | 77 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 74 | 63 |
| 28 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 78 | 63 |
| 29 | Male | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 72 | 83 |
| 30 | Female | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 75 | 83 |
| 31 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 77 | 80 |
| 32 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 77 | 53 |
| 33 | Male | ዳልቫ | 23 | 9ኛ | 73 | 77 |
| 34 | Female | ዳልቫ | 19 | 9ኛ | 76 | 90 |
| 35 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 73 | 63 |
| 36 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 76 | 93 |
| 37 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 76 | 73 |
| 38 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 78 | 90 |
| 39 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 74 | 70 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 40 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 76 | 83 |
| 41 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 79 | 70 |
| 42 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 72 | 67 |
| 43 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 76 | 70 |
| 44 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 71 | 70 |
| 45 | Male | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 70 | 60 |
| 46 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 78 | 53 |
| 47 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 75 | 57 |
| 48 | Male | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 70 | 67 |
| | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 49 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 72 | 67 |
| 50 | Female | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 75 | 67 |
| 51 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 72 | 60 |
| 52 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 69 | 67 |
| | | | | | | |
| 53 | Female | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 72 | 80 |
| 54 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 72 | 97 |
| 55 | Male | ዳልቫ | 17 | 9ኛ | 70 | 77 |
| 56 | Male | ዳልቫ | 18 | 9ኛ | 69 | 77 |
| 57 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 67 | 53 |
| 58 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 76 | 53 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 59 | Male | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 76 | 63 |
| 60 | Female | ዳልቫ | 16 | 9ኛ | 82 | 87 |
| | | አማካይ | | | 73.6 | 70.23 |

# አባሪ ስድስት

## የተማሪዎች የማንበብ ክሂል ፍላጎትና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት ተዛምዶ ስሌቶችን የሚያሳይ ማስረጃ፤

### Correlations

Descriptive Statistics

| | Mean | Std. Deviation | N |
|---|---|---|---|
| የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት | 73.60 | 3.362 | 60 |
| የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት | 70.23 | 11.272 | 60 |

Correlations

| | | የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት | የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|
| የማንበብ ክሂል | Pearson | 0.128 | .199 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መማር ፍላጎት | Correlation | | |
| | Sig. (2-tailed) | | .128 |
| | N | 60 | 60 |
| የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት | Pearson Correlation | .199 | .1 |
| | Sig. (2-tailed) | .128 | |
| | N | 60 | 60 |

Correlation is significant at the 0.128 level (2-tailed).

## T-Test

### Paired Samples Statistics

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት | 73.60 | 60 | 3.361 | .434 |
| | የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት | 70.23 | 60 | 11.272 | 1.455 |

**Paired Samples Correlations**

| | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|
| Pair 1 **የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት** | 60 | .199 | .128 |


Pair 1 **Paired Samples Test**

Paired Differences

| | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the | | T | Df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Lower | Upper | | | |
| **የማንበብ ክሂል መማር ፍላጎት እና የማንበብ ክሂል ፈተና ውጤት** | 3.367 | 11.103 | 1.433 | 0.498 | 6.235 | 2.349 | 59 | 0.022 |

# አባሪ ሰባት

## በትምህርት ቤቱ ለፈተና የተቀመጡ ተማሪዎች



ፎቶ አንድ




ፎቶ ሁለት




**ፎቶ ሦስት**

# አባሪ ስምንት

# ከተተኳሪ ትምህርት ቤት መረጃ ስልመውሰዱ የተሰጠ ደብዳቤ



ቁጥር 1050/92/16
ቀን 16/08/201

ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ የኢ/ያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ፡- የቆይታ ጊዜን ስለመስጠት ይሆናል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ተማሪ አስራት አሠፋ ሉታ በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ (የማንበብ ክህል ትምህርት መማር ፍላጎት እና በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ትምህርት ፈተና ውጤት ተዛምዶ ፍተሻ) በሚል ርዕስ እያካሄደ ላለው ጥናታዊ ጽሑፍ አስፈላጊውን ትብብር እንድናደርግላቸው ተጠቅሰው ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ የኢ/ያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል በቁጥር ኢ/ቋ/ሥ/አማ/836/16 በቀን 13/03/2016 ዓ/ም በተጻፈልን ደብዳቤ መሠረት በትምህርት ቤታችን ማለትም በዳልቻ ሁለተኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት ያደረገ መረጃዎችን ክፍሉን ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር በመሆን ስሰበሰብ ቆይተው የተመለሰ መሆኑን ለተማሪው ካለን መልካም ምኞታችን ጋር እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር!

Scanned with ACE Scanner